DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

ይህ *በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት እና የመቅረት ፖሊሲ (Attendance and Truancy Policy)*፤ ከዚህ ቀደም በዚህ ጉዳይ ላይ፣ በDCPS ታውጆ የነበረውን ሁሉንም ፖሊሲ፣ ሜሞራንዳ (memoranda)፣ እና/ወይም መመሪያ የሚሰርዝ እና የሚተካ ነው።

**ቻንስለሩ ያጸደቁት:** ______________________

**በስራ ላይ የዋለበት ቀን:** ኦክቶበር (October) 28 ቀን 2022

# በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (Attendance) እና የመቅረት (Truancy) ፖሊሲ

## I. ዓላማ እና የስፋት-መጠን

DCPS፣ ፀረ-ዘረኝነት የትምህርት ቤት ዲስትሪክ ለመሆን የሚሰራ፣ ይህም ቀውስ-ሲከሰት ምላሽ የሚሰጥ እና ለሁሉም ልጅን-በተመለከተ ጎን-ለጎን ሆኖ ለሚቀርብ አቀማመጥ ላይ - የእያንዳንዱ የልጅ-የየግል ሁኔታን እና ሁሉን-አቀፍ በሆነ-ሁኔታ፣ ትምህርት-ሰጪዎችን የሚረዳ ነው። ይህ ማለት፣ በመካከላቸው ያለ የዕድል ክፍተት የሚፈጥሩ ነገሮችን፣ የተቋማትን የተዛባ አመለካከትን ለማስቆም፣ እና ለቀለም-ትምህርት እና ለማህበራዊ ስኬቶች እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች የሚያስወገድ - በተለይ-ደግሞ ቀለም-ባላቸው ተማሪዎች (students of color) መካከል - ይህን-አካባቢ የሚፈጥር-ማለት ነው። DCPS፤ በተለይ የበለጠ የመለያየት ልዩነቶች በሚታዩባቸው ነገሮች ላይ የበለጠ እርዳታዎችን በመስጠት፤ የማግኘት ዕድል፣ አብሮ-መካተትን (inclusion)፣ እና ማረጋገጫን በመስጠት ላይ በንቃት-ለመስራት የሚገሰግስ ነው።

በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት (Attendance)፤ እንደ አጠቃላይ የልጅ፣ የፀረ-ዘረኝነት አቀራረብን ምልከታ-እንደሚያደርግ አንዱ-ክፍል ሆኖ የሚመለከት፤ ቁልፍ-የሆነ የመለኪያ-መንገድ ነው። በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት ፓተርኖች (Attendance patterns) - በልጁ ዕድገት ላይ ተጽዕኖ ሊያደርጉ-የሚችሉ ሌሎች ጎራዎች ላይ ተሞክሮዎች እንዲኖሩ፣ ቁልፍ-እይታዎችን የሚሰጥ ነው። ይህ ፖሊሲ፤ አጠቃላይ-የሆነ በትምህርት ገበታ-ላይ በመገኘት (attendance) ላይ መስፈርቶችን፣ ተማሪው ከትምህርት ቤት ካልተገኘ ወይም ከቀረ (truan) - የትምህርት ቤት ሹሞች የሚያስፈጽሙትን ፕሮቶኮሎች፣ እና በዲሲ ጤና የክትባት በግዳጅ-መወሰድ-ያለባቸውን ከማስፈጸም ጋር ተዳዳኝ-የሆኑ ነገሮችን፤ ይህ-ፖሊሲ ያከብራል።

## II. ሥልጣን እና በስራ ላይ የሚውል ሕግ (AUTHORITY AND APPLICABLE LAW)[1]

| **ምንጭ** | **ጥቅስ (Citation)** |
|---|---|
| የኮሎምብያ ዲስትሪክት ሕግ | - D.C. Official Code § 38-202 – የትምህርት ቤት በትምህርት-ገበታ የመገኘት (attendance) መስፈርቶችን መመስረት<br>- D.C. Official Code § 38-236.04 – እንዳይገኙ መከልከል (exclusion)ን እንደ የስነ-ስርዓት መቅጫ እርምጃ አድርጎ መጠቀምን-ውሱን ማድረግ<br>- D.C. Official Code § 38-501, *et seq.* – የትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ክትባት (Immunization) |
| የኮሎምብያ ዲስትሪክት የማዘጋጃ ቤት ደንቦች | የዲሲ የስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (DC Office of State Superintendent of Education (OSSE)<br>- 5-A DCMR § 2100 – አጠቃላይ አቅርቦቶች - በ'OSSE የአስቸኳይ-ጊዜ እና እንዲደረግ-ሃሳብ በቀረበው ደንብ-ማውጣት (OSSE Notice of Emergency and Proposed Rulemaking) በተስተካከለው-መሠረት፤ 69 DCR (Sept. 16, 2022)<br>- 5-A DCMR § 2101 – በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት (attendance) መዝገቦች፣ እና ሪፖርት-ማድረግ - በ'OSSE የአስቸኳይ-ጊዜ እና እንዲደረግ-ሃሳብ በቀረበው ደንብ-ማውጣት (OSSE Notice of Emergency and Proposed Rulemaking) በተስተካከለው-መሠረት፤ 69 DCR (Sept. 16, 2022)<br>- 5-A DCMR § 2102 – መቅረቶች (Absences) - በ'OSSE የአስቸኳይ-ጊዜ እና እንዲደረግ-ሃሳብ |

[1] በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ያለ ምንም-ነገር፣ የፌደራል፣ ስቴት፣ ወይም የአካባቢው (local) ሕግን - አይተካም።

| | |
|---|---|
| | በቀረበው ደንብ-ማውጣት (OSSE Notice of Emergency and Proposed Rulemaking) በተስተካከለው-መሠረት፤ 69 DCR (Sept. 16, 2022)<br>- 5-A DCMR § 2103 – በቀረዎች-ላይ ጣልቃ-ገብነት እና በትምህርት ቤት ላይ-መሠረት ያደረገ - የተማሪ የእርዳታ ቡድኖች - በ'OSSE የአስቸኳይ-ጊዜ እና እንዲደረግ-ሃሳብ በቀረበው ደንብ-ማውጣት (OSSE Notice of Emergency and Proposed Rulemaking) በተስተካከለው-መሠረት፤ 69 DCR (Sept. 16, 2022)<br>- 5-A DCMR § 2199 – ትርጓሜ (Definitions) - በ'OSSE የአስቸኳይ-ጊዜ እና እንዲደረግ-ሃሳብ በቀረበው ደንብ-ማውጣት (OSSE Notice of Emergency and Proposed Rulemaking) በተስተካከለው-መሠረት፤ 69 DCR (Sept. 16, 2022)<br><br>የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS)<br>- 5-B DCMR § 2103 - መቅረት (Truancy)<br><br>ዋናው/ኦሪጅናል ታይትል (Original Title) 5<br>- 5-E DCMR § 2101 – መቅረቶች (Absences)<br>- 5-E DCMR § 5300 – የሕዝብ ትምህርት ቤት የክትባት (Immunization) ሂደቶች እና መስፈርቶች |

## III. ቁልፍ-የሆኑ አባባሎች እና ትርጉሞቻቸው[2]

**መቅረት (Absence)** ማለት፤ በትምህርት ቀን ውስጥ - ተማሪው ሙሉ-በሙሉ ወይም በከፊል በሚቀርበት-ጊዜ ማለት ነው።[3] ከዚህ-በታች፣ በዚህ ፖሊሲ ውስጥ በተጨሪ እንደተገለደው ሁሉ፤ DCPS፣ ፈቃድ-ባገኘ (excused) እና ፈቃድ-ባላገኘ (unexcused) መቅረቶች መካከል ያለውን-ልዩነቶች ለይቶ-ያስቀምጣል።

**በተደጋጋሚ-መቅረት (Absenteeism)** ማለት፤ ከፍተኛ ተደጋጋሚነት ያለው የመቅረት ፓተርን (pattern) ማለት-ነው።[4]

**ከመደበኛ-ውጪ የሚከናወን የርቀት የትምህርት-አሰጣጥ (Asynchronous Distance Instruction)** ማለት፤ ጎን-ለጎን በሆነ መንገድ የማይሰጥ (non-simultaneous) የርቀት ትምህርት-አሰጣጥ ሲሆን፣ አስተማሪው በእውነተኛ-በዚያኑ ጊዜ (real time) የሚሰጥ የትምህርት አሰጣጥ ሳይኖር-ተማሪው ለብቻልው ስራውን ሰርቶ-የሚያጠናቅቅበት ማለት ነው።[5]

**በትምህርት ገበታ ላይ መገኘትና አለመገኘት ላይ እርምጃ ዕቅድ (Attendance Action Plan)** ማለት፤ አንድን-ግለሰብን እና የተማሪውን በልዩ ሁኔታ የሚያስፈልጉትን ሊያሟላ እንዲችል ተደርጎ የተቀረጸ የጽሁፍ-ሰነድ እና፣ የተማሪውን አስፈላጊ የሆኑ በትምህርት ገበታ መገኘት (attendance) ሰነድን ዝርዝር የያዘ፣ የሚጠበቀውን የትምህርት ገበታ ላይ መገኘት (attendance) ግቦችን፣ በትምህርት ቤት ላይ መሠረት ያደረገ ወይም ሦስተኛ-ወገን/third-party-አገልግሎት ሰጪ-የሆነን ጣልቃ-ገብነቶች - በትምህርት ቤት ውስጥ መሠረት ባደረገው የተማሪ እርዳታ ቡድኑ አማካኝነት በተወሰነው - ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች (unexcused absences) ላይ -ይህን ችግር ፈጣሪ የሆኑትን ችግሮች መፍትሄ በማስገኘት ላይ የሚያገለግል ማለት ነው።[6]

---

[2] ለ'Chapter 21' ላይ ላሉ ሁሉም-ጥሰቶች - (Compulsory Education and School Attendance), Subtitle A (Office of the State Superintendent of Education) of Title 5 (Education), of the District of Columbia Municipal Regulations (DCMR) are citations to 5-A DCMR Chapter 21, as amended by OSSE Notice of Emergency and Proposed Rulemaking, 69 DCR (Sept. 16, 2022).
[3] *See* 5-A DCMR § 2199.1.
[4] *See* 5-A DCMR § 2199.1.
[5] *See* 5-A DCMR § 2199.1.
[6] *See* 5-A DCMR § 2199.1.

## በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (Attendance) እና የመቅረት (Truancy) ፖሊሲ

**በትምህርት ገበታ መገኘት ካውንስለር/ተወካይ (Attendance Counselor/Designee)** ማለት፤ በርዕሰ መምህሩ - የሚከተሉትን ኃላፊነቶች እንዲወጣ የተመደበ አንድ-ሰው(ዎች) ሲሆኑ፤ የተማሪዎችን በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት (attendance)ን ለማሻሻል፣ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በመደበኛ ሁኔታ መገኘታቸውን ማረጋገጥ፣ የተማሪውን በትምህርት ገበታ ላይ መገኘትን ለመጨመር እና በመቅረት ላይ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ - የትምህርት ገበታ ላይ መገኘት ጣልቃ-ገብነቶች/interventionsን ለማስተባበር እና ለመከታተል የሚመደብ-ሰው/ዎች ማለት ነው።

**የትምህርት ገበታ ተቆጣጣሪ (Attendance Monitor)** (የትምህርት ገበታ/attendance የግንኙነት-ተወካይ (point-of-contact (POC) ተብሎም ይታወቃል) ማለት፤ በትምህርት ተቋሙ ርዕሰ መምህር፣ በሚከተሉት ላይ ኃላፊ እንዲሆን የተመደበ ሰው(ዎች) ማለት ሲሆን፤ ለኮሎምብያ ዲስትሪክት ለትምህርት እና የትምህርት ቤት በትምህርት-ገበታ መገኘት ሕጎችና፣ ደንቦች እና የOSSE ፖሊሲዎች - በግዳጅ ማሟላት የሚያስፈልጉትን -በእያንዳንዱ የትምህርት ተቋም ውስጥ ገብቶ ለሚማር ተማሪ - የትምህርት ገበታ ሰነዶችን - መሰብሰብ፣ መጠበቅ እና ሪፖርት የሚያደርግ ግለሰብ/ቦች ማለት ነው።[7]

**ስር-የሰደደ መቅረት (Chronically Truant)** ማለት፤ አስገዳጅ ዕድሜ ውስጥ ለሆነ ተማሪ - በD.C. Official Code § 38-202(a) እንደተደነገገው፤ አስር (10) ወይም ከዚያ በላይ ቀናቶችን፣ ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች - በአንድ የትምህርት-ዓመት ውስጥ የሚገኝበት-ሁኔታ ማለት ነው።[8]

**ሙሉ የትምህርት ቀን** ማለት፤ አጠቃላይ የትምህርት አሰጣጥ ሰዓታቶቹ በመደበኛነት በአንድ የትምህርት-ቀን ውስጥ የሚሰጠው-ማለት ነው።[9]

**ሙሉ-ለሙሉ መቅረት (Fully Absent)** ማለት፤ ለተመደበው የትምህርት ቀን፣ ተማሪው - ለአጠቃላይ የትምህርት-አሰጣጥ ቀኑ - በትምህርት-ገበታ ላይ በማይገኝበት ጊዜ፤ ማለት ነው። ይህ ስያሜ፤ ለሁለቱም - ፈቃድ-ላገኘው (excused) እና ፈቃድ-ላላገኘው (unexcused) - ለሙሉ የትምህርት ቀኑ መቅረቶች፤ በስራ-ላይ የሚውል ነው።[10]

**ሙሉ-ለሙሉ መገኘት (Fully Present)** ማለት፤ ለተመደበው የትምህርት ቀን፣ ተማሪው - ለአጠቃላይ የትምህርት-አሰጣጥ ቀኑ - በትምህርት-ገበታ ላይ በሚገኝበት ጊዜ፤ ማለት ነው።[11]

**በቦታው-ላይ መገኘት (In-Seat Attendance)** ማለት፤ ተማሪው በትምህርት ቤት የተገኘበት ቀናት - በመቶኛ/percent ሲሰላ-ማለት ነው።

**ሞጁል (Module)** ማለት፤ የትምህርት-አሰጣጥ ቀኑ ንዑስ ክፍል (subdivision) ሲሆን፣ እንደ የመማሪያ ክፍለጊዜ (class period) ወይም ለትምህርታዊ-ሂደት የተገደበ፤ ማለት ነው።[12]

**'MTSS'** ማለት፤ 'a multi-tiered system of supports' ለትምህርት-ሰጪዎች፣ የትምህርት ቤት አመራሮች፣ እና የዲስትሪክት መሪዎች - ያሏቸውን በመማር ላይ ያሉትን እንቅፋቶች - በዘዴዎች ደረጃ (systems level) ለማስወገድ፣ ማስረጃ-ላይ መሠረት ያደረጉ ልምምዶችን በአጠቃላይ ልጁን ከ' tiered continuum' ጋር ለመርዳት ጥቅም-ላይ የሚውል፣ እና በመረጃ-ስብስብ ላይ መሠረት ያደረጉ - ዒላማ-ለተደረገለት እና ጠንከር-ብሎ ለሚሰጡ  የጣልቃ-ገብነቶች ውሳኔዎችን ለመውሰድ የሚያገለግሉ-ማለት ነው።

---

[7] *See* 5-A DCMR § 2199.1.
[8] *See* 5-A DCMR § 2199.1.
[9] *See* 5-A DCMR § 2199.1.
[10] *See* 5-A DCMR § 2199.1.
[11] *See* 5-A DCMR § 2199.1.
[12] *See* 5-A DCMR § 2199.1.

**የ'MTSS የአመራርነት-ቡድን** ማለት፤ የሠራተኛ-አባላቶች ስብስብ ቡድን ሆኖ፣ ይህም ሊያካትት የሚችለው፤ ርዕሰ መምህር፣ ረዳት ርዕሰ መምህር፣ ካውንስለር፣ ማህበራዊ-ሠራተኛ፣ የስነ-ልቦና ሠራተኛ (psychologist)፣ የትምህርት ቤት ነርስ፣ አስተማሪዎች፣ የልዩ ትምህርት (special education) ሠራተኛ፣ በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance) ካውንስለር እና/ወይም በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት ተወካይ (attendance designee) - የ'MTSS'ን በትምህርት ቤት ውስጥ የሚመራውን፤ ሊያካትት ይችላል።

**የዲሲ የስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of the State Superintendent of Education (OSSE)** ማለት፤ የስቴት ለኮሎምብያ ዲስትሪክት - የትምህርት ድርጅት (State Education Agency (SEA) - በስቴት የትምህርት ቢሮው (State Education Office) 2000 ድንጋጌ፣ ከኦክቶበር (October) 21, 2000 ጀምሮ የተመሰረተ (D.C. Official Code §§ 38-2601 et seq.)፤ በD.C. Official Code § 38-2652 የስቴት የትምህርት ቦርድ (State Board of Education) በስተቀረ፤ በሁሉም በስቴት-ደረጃ ክንውኖችን ስልጣን የሚሰራ ማለት ነው።

**ውጤት (Output)** ማለት፤ በተማሪው የርቀት ትምህርት አሰጣጥ ሞጁል ወቅት የተጠናቀቀውን እንቅስቃሴ - በሞጁሉ ውስጥ የተሰጠውን የትምህርት-አሰጣጥ የሚያንጸባርቅ ማለት ነው።[13]

**ወላጅ (Parent)** ማለት፤ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ወይም ሌላ ሰው በኮሎምብያ ዲስትሪክት ውስጥ የሚኖሩ-እና የማሳደግ-ኃላፊነት ወይም የታዳጊ-ልጁ (minor) ቁጥጥር የተሰጠው-ሰው ማለት ነው።[14]

**በከፊል መቅረት (Partially Absent)** ማለት፤ የትምህርት ቀን ተብሎ በተሰየመው ቀን፣ ተማሪው - ከ60 በመቶ ባነሰ ጊዜ ለትምህርት-አሰጣጥ ቀኑ በሚገኝንገት-ጊዜ፤ ማለት ነው። ይህ ለሁለቱ - ፈቃድ-ላገኘው (excused) እና ፈቃድ-ላላገኘው (unexcused) መቅረት/absence፤ በስራ-ላይ ይውላል።[15]

**በከፊል መገኘት (Partially Present)** ማለት፤ የትምህርት ቀን ተብሎ በተሰየመው ቀን፣ ተማሪው - ከ60 በመቶ ባነሰ ጊዜ - የቀረበት-ክፍለ ጊዜ ፈቃድ-ያገኘ የነበረ (excused) ሆነም-አልሆነ፤ ለትምህርት-አሰጣጥ ቀኑ በሚገኝበት-ጊዜ፤ ማለት ነው።[16]

**መገኘት (Present)** ማለት፤ በትምህርት ቀን ውስጥ - ተማሪው ሙሉ-በሙሉ ወይም በከፊል - በሚገኝበት-ጊዜ፤ ማለት ነው።[17]

**ተገልሎ-መቆየት/ኳራንቲን (Quarantine)** ማለት፤ በአካል-ተገኝቶ ከሚሰጠው የትምህርት አሰጣጥ ውስጥ እና ከሌሎች እንቅስቃሴዎች ውስጥ፤ ከኮሎምብያ ዲስትሪክ ባለስልጣናት ትዕዛዝ መሠረት - ባለው ተላላፊ በሽታ፣ ብክለት (infection)፣ ተወርሮ-መበከል (infestation)፣ ወይም ሌላ ከሌሎች ተማሪ በሕክምና ወይም ለጤና ምክንያቶች መለየት የሚገባው ሁኔታ ሲፈጠር፤ ተገልሎ-የሚለይበት ሁኔታ፤ ማለት ነው።[18]

**ዘወትር-በተደጋጋሚ የሚደረግ የርቀት የትምህርት አሰጣጥ (Routine Distance Instruction)** ማለት፤ የትምህርት አሰጣጡን፣ በትምህርት ቤት በመደበኛነት ወይም በሌላ አቀማመጥ መሠረት በማድረግ ከትምህርት ቤት ውጪ -

---

[13] *See* 5-A DCMR § 2199.1.
[14] *See* 5-A DCMR § 2199.1.
[15] *See* 5-A DCMR § 2199.1.
[16] *See* 5-A DCMR § 2199.1.
[17] *See* 5-A DCMR § 2199.1.
[18] *See* 5-A DCMR § 2102.2(b).

ከተማሪው በካል የሚገኝበት የትምህርት ቤት ህንፃ ውጪ - በርቀት (virtual) የትምህርት አሰጣጡ ሞዴል አንዱ-አካል በመሆን ለመስጠት ጥቅም-ላይ የሚውል የትምህርት አሰጣጥ ማለት ነው።[19]

**ሁኔታዎችን ያገናዘበ የርቀት ትምህርት (Situational Distance Learning)** ማለት፤ የተወሰነ-የጊዜ ገደብ ሆኖ ትምህርት-ቤቱ -አስገዳጅ በሆኑ ሁኔታዎች የትምህርት አሰጣቱን በአንዳንድ ጊዜያዊ፣ የአስቸኳይ-ጊዜ ሁኔታ አስፈላጊነት ምክንያት መስጠት በሚከለክልበት ጊዜ፣ የመማሪያ-ክፍሉን፣ የክፍል-ደረጃን፣ ወይም አጠቃላይ ትምህርት ቤቱን ወደ የርቀት ትምህርት (distance learning) ሊያሸጋግረው ይችል-ይሆናል። እንዲህ-ዓይነቱ ሁኔታ፣ ቀደም-ተብሎ ያልታቀደን ነገር በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች (ማለትም፤ በሕዝብ ጤና ምላሽ መስጠት፣ በክንውናዊ ጉዳዮች፣ አስቸጋሪ-የሆነ የአየር-ጠባይ፣ ወዘተ…) ምክንያት ምላሽ-ሊሰጥበት የሚያስፈልግ ይሆናል። ትምህርት ቤቱ እንደነዚህ ያሉ የአስቸኳይ ጊዜ የክንውናዊ ሁኔታዎች መኖራቸውን ከወሰነ - የትምህርት ቤት አመራሮች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው: ለውጡን-ለማድረግ ከትምህርት አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጁ ፈቃድ-ማግኘት አለባቸው፤ (በርዕሰ-መምህራን የስልጣን-ደረጃ ውስጥ ለሆኑ የክፍል-ደረጃዎች ዝውውሮች ካልሆነ-በስተቀረ) እና፣ አንድ-ጊዜ ፈቃዱን ካገኙ በኋላ፣ ወዲያውኑ ወላጆችን እና ሠራተኞችን ስለ ለውጡ ወደ ሁኔታዊ የርቀት ትምህርት መዛወር ያሳውቃሉ፣ ተማሪዎች ለመማሪያ መሣሪያዎች በቂ የማግኘት አቅም-እንዳላቸው ያረጋግጣሉ፣ ቀኑን - በ‘eSchoolPLUS’ ላይ - እንደ “Situational Distance Learning” ቀን አድርገው-ይመዘግባሉ። ትምህርት ቤቱ - ይህን ተለዋዋጭነት ያለው ሁኔታ፣ በትምህርት ዓመቱ ወቅት - እስከ አምስት (5) አጠቃላይ የትምህርት ቀን - በተከታታይም ሆነ እያለፈ-እያለፈ የሚመጣ ቢሆን - ካለ ምንም-ፈቃድ ማግኘት ሊጥቀሙ-ይችላሉ። ዲስትሪክቱ፣ የሁኔታዊን የርቀት ትምህርትን ከአምስት (5) ቀናት በላይ ለመጠቀም ከፈለገ፤ ከአምስት (5) ቀናት በላይ ለመሄድ - የትምህርት ቤቱ አመራሮች ማንሻ (waiver) መጠየቅ-አለባቸው።[20]

በሁኔታዊያዊ የርቀት መማር (situational distance learning) ውስጥ - ተማሪው ተገኝቷል/present ብሎ ከግምት-ውስጥ ለማስገባት፣ ትምህርት ቤቱ የሚከተሉትን ማድረግ-ለበት:

1. የተማሪውን መገኘት፤ ትክክለኛነት ማረጋገጥ። ይህ በበርካታ ዓይነት መንገዶች መከናወን የሚችል-ይሆናል፤ ለምሳሌ፣ ተማሪው ወደ መማሪያ መቆጣጠሪያ ዘዴው - በማንኛውም የግንኙነት/communication መንገዶች-(እንደ ቴክስት/text፣ ስልክ፣ ካሜራ፣ ወዘተ…) ባሉት አማካኝነት መግባቱን በማረጋገጥ፤ እና
2. በየሁኔታዊያዊ የርቀት መማር ቀኑ (situational distance learning day) ላይ፣ ቢያንስ አንድ ወይም ከዚያ-በላይ ሰርቶ-በማጠናቀቅ የሚያስገባቸው ነገር እንዲኖሩ በማረጋገጥ፤ ነው።

**መደበኛ ባልሆነ-መንገድ የሚሰጠውን ትምህርት (Synchronous Learning)** ማለት፤ የቀለም-ትምህርት አቀማመጥ ሆኖ - ማስተማር እና መማሩ የሚካሄደው ወዲያውኑ-ጎን ለጎን ሆኖ በሚሰጥ ሁኔታ (simultaneously) ይኸውን፣ አስተማሪው በዚያኑ ጊዜ - እርምጃ መውሰድ እና ምላሽ መስጠት የሚችልበት ሲሆን ተማሪዎችም እንደዚሁ በዚያኑ ጊዜ እንደዚሁ ለማድረግ የሚችሉበት ሁኔታ ነው።[21]

**የተማሪ በትምህርት ገበታ ላይ መገኘና አለመገኘት ኮንፈረንስ (Student Attendance Conference)** (SAC) ማለት፤ ስብሰባው በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት ካውንስለር (Attendance Counselor)/ወኪል (Designee)፣ ወላጅ/አሳዳጊ፣ እና በተማሪ (እንደ አስፈላጊነቱ) ጋር፣ ግለሰብ ተማሪውን የትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት የእርምጃ ዕቅዶችን በማዘጋጀት እና በማስፈጸም፤ እና የጣልቃ-ገብነት ስልቶችን - በትምህርት ቤት ወይም በማህበረሰብ-ላይ ያተኮረውን ለማካሄድ፣ እና እና የተማሪውን ስኬታማነት ለማሳደግ የተቀረጸውን በማረብ ተማርውን ለመርዳት የሚደረግ ነው።[22] ‘SAC’ -

---

[19] *See* 5-A DCMR § 2199.1.

[20] *See* 5-A DCMR §§ 2101.11—2101.17.

[21] *See* 5-A DCMR § 2199.1.

[22] *See* 5-A DCMR § 2103.4 and D.C. Official Code § 38-201(3B). ‘SAC’ - በትምህርት ቤት መሠረት-ያደረገ የተማሪ-እርዳታ ቡድን ኃላፊነቶችን - የሚያሟላ-ነው።

በአካል-ተገኝቶ ( in-person)፣ በስልክ-አማካኝነት፣ ወይም በቪዲዮ ኮንፈረንስ-አማካኝነት ሊካሄድ ይችላል።

**ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች (Unexcused Absence)** ማለት፤ በተመደበው ቀን ላይ ተማሪው በሙሉ-ቀን መቅረት ወይም በከፊት-በመቅረት፤ ምንም-ሕጋዊ የሆነ ምክንያት ሳይኖረው፤ መቅረት ማለት-ነው።[23]

## IV. መስፈርቶች

### A. አጠቃላይ - የትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘት (Attendance) መስፈርቶች

በአሁኑ የትምህርት ዓመት ውስጥ - ከሴፕቴምበር (September) 30 ቀን በፊት - ዕድሜያቸው አምስት (5) ዓመት የሞላቸው ሁሉም ልጆች፤ ለትምህርት ዕድሜያቸው የደረሰ ተብለው ከግምት-ውስጥ የሚገቡ እና በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤት ተገኝተው እስከ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የምርቃት (Graduation) መስፈርቶች እስከሚደርሱ ድረው፤ ወይም እስከ 18 የልደት-በዓላቸው ድረስ መማር አለባቸው።[24,25]አንድ-ጊዜ በቅድመ-መዋዕለሕፃናት (Pre-K) ተማሪዎች እንደ የDCPS ተማሪዎች ሆነው ከተመዘገቡ - እንደ ማንኛውም ለትምህርት-የደረሱ ትተማሪዎች አንድ-አይነት በሆነ ሁኔታ በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት ፖሊሲዎች (attendance policies)ን - ሰዓቱን-ጠብቆ በትምህርት ቤት ውስጥ መገኘትን ጨምሮ ህጉን መከተል-ይጠበቅባቸዋል።

ለአቅመ-አዳም ያልደረሱ (Minors) - ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተመረቁ፤ ከዚያ በኋላ በትምህርት ቤት ውስጥ ገብተው መማር አያስፈልጋቸው።[26] አስራ-ሰባት (17) ዓመት ዕድሜ ላይ ለደረሱ ተማሪዎች፣ ወደ-ምርቃት በትክክለኛው መንገድ ላይ የሚገኙ፣ እና መደበኛ-የሆነ ጥቅም-የሚያስገኝ ቅጥር-እንደነበራቸው ሰነዶችን ማቅረብ-ለሚችሉ፤ ተለዋዋጭነት-ያለው የትምህርት ቤት ሰዓታት ሊፈቀድላቸው ይችላል።[27]

### B. ከትምህርት ቤት የሚጠበቁ-ነገሮች

ሁሉም ትምህርት ቤቶች፤ የተለየ ፕሮቶኮልን - በትምህርት ገበታ ላይ መገኘትን (attendance) እና ተደጋጋሚ-መቅረቶችን (absenteeism) ለመቆጣጠር - ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች (unexcused absences)ን በመከላከል-ላይ ትኩረት ማድረግ እና የተማሪዎችን ፍላጎቶች ምላሽ-ለመስጠት የቀለም-ትምህርት እና የባህሪያዊ ጣልቃ-ገብነቶችን በማካሄድ ላይ ትኩረት ማደረግን ጨምሮ - ማስፈጸም-አለባቸው። የትምህርት ቤት ሠራተኛ-ሹሞች፤ በትምህርት ገበታ-ላይ የመገኘት

---

[23] *See* 5-A DCMR § 2102.1.

[24] የD.C. Official Code § 38-202 አስገዳጅ-በሆነ የተማሪዎች ዕድሜ፣ በመደበኛነት በትምህርት ገበታ መገኘት መስፈርትን፤ ተመልከቱ። መደበኛ-በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት የሚያካትተው፤ ወደ ትምህርት ቤት በሰዓቱ-መድረስንም ነው።

[25] የ5-E DCMR § 3002.1(d)ን በመከተል፤ ለልዩ ትምህርት (special education) በDCPS ብቁ-ሆኖ የተገኘ ልጅ፤ እስከ ሴሚስተሩ መጨረሻ - ዕድሜያቸው 22 እስከሚሆን ድረስ፤ አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ-ይሆናል።

[26] D.C. Code Official Code § 38-202(b) (“የሲኒየር ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የኮርስ ጥናቱን - በ [DCPS] የሚሰጠውን በአጥጋቢ-ሁኔታ ያጠናቀቀ ማንኛውም ለአቅመ-አዳም ያልደረሰ (minor)፣ እና ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መመረቁን ወይም መመረቋን ለማረጋገጥ ዲፕሎማ የተሰጥው/ጣት ከሆነ፣ ወይም በ [DCPS] በተወሰነው መሰረት በሌላ ጥናት ኮርስ ማረጋገጫ ወይም ዲፕሎማ ያለው እና በ [DCPS] ከሕዝብ ሲኒየር ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለመመረቅ፣ አነስተኛ-የሆነውን የሚስተካከል ደረጃ ቢያንስ ያለው፣ ወደፊት ከሚኖረው በትምህርት ገበታ-ላይ መገኘት/attendance ፈቃድ-ያገኘ ሊሆን ይችላል።”).

[27] *See* D.C. Official Code § 38-202(b)(“ማንኛውም የ17 ዓመት ዕድሜ ላይ የደረሰ ለአቅመ-አዳም ያልደረሰ (minor)፣ ለአቅመ-አዳም ያልደረሰ (minor) በሚማርበት ውስጥ በሚገኘው የትምህርታዊ ተቋማት ዋና መሪ፣ እርሱ ወይም እርሷ በእርግጥ፣ በሕጋዊነት፣ በማግኘት-ሙብት፣ እና በመደበኛነት በመቀጠር፤ ለተለዋዋጭነት ላለው የትምህርት ቤት ሰዓታት ማግኘት ሊፈቀድለት/ላት ይችል-ይሆናል፤ ነገር ግን በምንም-ዓይነት ሙሉ ለሙሉ ከአጠቃላይ መደበኛ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (attendance) ፈቃድ ማግኘት፣ ወይም የእርሱ ወይም የርሷን የምርቃት ጊዜን ሊያበላሽ ወይም ሊከለክል በሚችሉ ሁኔታ ፈቃድ-የሚያገኙበት ሁኔታ አይኖርም።”). ተቀጣሪ-ለሆኑ ተማሪዎች፤ የግማሽ-ቀን የጊዜ ሰሌዳዎችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፤ በ5-B DCMR § 2103.2 እና በ5-E DCMR § 2101.2 ላይ ተመልከቱ።

ቁጥጥርን በትክክለኛነት በየቀኑ በመውሰድ - በተማሪው የመረጃ ዘዴ (student information system (SIS) ውስጥ በትክክል ማስገባት ወይም በDCPS በቀረቡ አማራጭ-መንገዶች አማካኝነት ማስገባት አለባቸው። የትምህርት-ገበታ ላይ መገኘትን በመረጃ-ለመመዝገብ - ተጨማሪ መስፈርቶች፣ እና ለርቀት የመማር ሞዴሎች - በትምህርት-ገበታ ላይ ስለመገኘት የሚጠበቁትን ነገሮች፤ በ'Appendix A' ቀርበዋል።

የትምህርት ዓመቱ ከመጀመሩ-አስቀድሞ፣ የሁሉም ትምህርት ቤት ርዕሰ-መምህራኖች - በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘትና አለመገኘት የግንኙነት-ተወካይ (point-of-contact (POC) የሆነን ሰው መወከል-አለባቸው። በ'Central Services Attendance Team' ትዕዛዝ -መሠረት፤ በትምህርት ገበታ ላይ መገኘትና አለመገኘት የግንኙነት-ክፍል ሠራተኛ (attendance POC) - በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት (Attendance) መዝገቦችን ጊዜውን በጠበቀ መልኩ ማስገባት፣ ማንኛውም የተስተካከለ በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት (Attendance) መዝገቦችን በአስራ-አምስት (15) የስራ-ቀናቶች ውስጥ ማስገባት፣ እና ስለገቡት በትምህርት ገበታ ላይ ስለመገኘት ሰነዶች ላይ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ጊዜውን-በጠበቀ መንገድ ምላሾችን መስጠት አለባቸው።

የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራኖች፤ የትምህርት-ገበታ ተወካይ የሆነን ሰው (attendance designee) - የተማሪዎችን በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት (attendance)ን ለማሻሻል፣ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በመደበኛ ሁኔታ መገኘታቸውን ለማረጋገጥ፣ የተማሪውን በትምህርት ገበታ ላይ መገኘትን ለመጨመር እና በመቅረት ላይ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ - በዚህ ፖሊሲ የሚያስፈልገውን - የትምህርት ገበታ ላይ መገኘት ጣልቃ-ገብነቶች/interventionsን ለማስተባበር እና ለመከታተል ይህን-ተወካይ መመደብ-አለባቸው። ትምህርት ቤቱ - በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት ካውንስለር (attendance counselor) ካለው፤ የትምህርት-ገበታ ላይ ተወካይ (attendance designee) የስራ-ድራሻን በተልምዶ-የሚያከናውኑ ሲሆን (በዚህም-ምክንያት፤ ይህ የስራ ድርሻ በዚህ ፖሊሲ ውስጥ እንደ 'Attendance Counselor/Designee, ወይም AC/AD ተብሎ ተጠቅሷል)፤ ሆንም-ግን አስፈላጊ አይደለም። እንደ በትምህርት-ገበታ የመገኘት የግንኙነት ሠራተኛ (attendance POC) ሆኖ የተመደበው ግለሰብ፤ እነዚህም ኃላፊነቶች - እንደ በትምህርት-ገበታ ተወካይ (attendance designee) ሆኖ ሊያከናውን ይችላል።

አስተማሪዎች፤ ዕለታዊ በትምህርት ገበታ መገኘትን (daily attendance) - ለመጀመሪያ ደረጃ-ትምህርት ቤቶች እና ለእያንዳንዱ የሁለተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤቶች፤ በአስፐን (Aspen) ውስጥ - መውሰድ እና ማስገባት አለባቸው። የትምህርት ቤት ህንፃውን ወይም የመማሪያ-ክፍሉን ዘግይቶ የገባ ማንኛውም ተማሪ፤ በአስፐን (Aspen) ውስጥ እንደ አርፋጅ (as tardy) ሆኖ እንጂ እንደ ቀሪ ሆኖ አይመዘገብም። በትምህርት ገበታ-ላይ መገኘትና አለመገኘት (Attendance)፤ የትምህርት ቀኑ ከማለቁ በፊት በትክክል-ገብቶ መጠናቀቅ እና አዲሱ መረጃ እንደታወቀ፤ በየቀኑ-አዲስና ማሻሻያ (update) መደረግ አለበት።

### C. ፈቃድ-ያገኘ መቅረቶች (Excused Absences) እና አስፈላጊ-የሆኑ ሰነዶች

መቅረቱ-ፈቃድ እንዲያገኝ ለማድረግ፤ በተማሪው ወላጅ ወይም አሳዳጊ - ከበከፊል ወይም የሙሉ-ቀን መቅረቡ አስቀድሞ፤ ወይም በ አምስት (5) የትምህርት ቀናት ተማሪዎ በከፊት ወይም የሙሉ-ቀን መቅረትን አድርጎ ከተራዘመ-የትምህርት ቤት መቅረትን ካደረገ በኋላ ወደ ትምህርት ቤት ሲመለስ፤ የጽሁፍ ማስታወሻን ለትምህርት ቤቱ ማቅረብ አለበት።[28] የጽሁፍ ማስታወሻዎቹ፤ በኢሜል፣ በቴክስት መልዕክቶች (text messages)፣ እና በሌላ የጽሁፍ የኤሌክትሮኒክስ-መገናኛ አማካኝነት መግባት አለበት። ተገቢ የሆነ ማስታወቂያ እና ተጨማሪ ሰነድ - አስፈላጊ ለሆነ - በአምስት-የትምህርት ቀን የጊዜ-ገደብ ውስጥ ከቀረበ፤ ትምህርት ቤቱ የቀረበትን ምክንያት እንደ ፍቃድ የተሰጠው እንደሆነ አድርጎ አስተካክሎ በ48 ሰዓታት ውስጥ ማስተካከያ-ማድረግ አለበት።

[28] *See* 5-E DCMR § 2101.4 ("ተማሪው የቀረበትን ምክንያት የሚገልጽ-ጽሁፍ - ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት በተመለሰበት ቀን ላይ እንደሚያቀርቡ የወላጅ ወይም የአሳዳጊ የጽሁፍ ማረጋገጫ።"); 5-A DCMR § 2102.4 ("የትምህርት ቤት ተቋሙ - ተማሪዎ ከትምህርት ቤት የቀረበትን ምክንያት ማረጋገጫ - ከወላጅ ወይም አሳዳጊው የጽሁፍ-ገለፃ እንዲያቀርብ መጠየቅ አለበት፤ እና ይህ የጽሁፍ ገለጻ፣ ተገቢ-ከሆነ - በቅድሚያ-ማቅረብ አለባቸው፣ እና ቀድሞ-ሊቀርብ ካልቻለ፤ ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት በተመለሰ ጊዜ መቅረብ አለበት።").

ሁሉም የጽሁፍ ማስታወሻዎች፤ የሚከተሉት **መያዝ-አለባቸው**:

1. ቀን-መፃፍ-አለበት፤
2. የመቅረቱ (absence)ን ምክንያት ያካተተ-መሆን፣ እና
3. ተማሪዎ ከትምህርት ቤት ውጪ የነበረበትን፣ ወይም የሚሆንበትን የተወሰኑ-ቀናቶችን ማካተት።

ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ያላሟሉ ማስታወሻዎች (Notes)፤ ከግምት-ውስጥ ገብተው ለጥቅም-አይውሉም።

በ'504 plan' እና/ወይም በ 'Individualized Education Program (IEP)' ውስጥ እየተደገፉ ያሉ ተማሪዎች ያሏቸው ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች፤ እነርሱም-ቢሆኑ ለተማሪው መቅረት(ቶች) ከ5-ቀን የጊዜ-ገደብ ውስጥ ምክንያቱን ፈቃድ-ማግኛ ምክንያት ዝርዝር የያዘ ማስታወሻ-ማስገባት አለባቸው።

ከ40% ወይም ከዚያ በላይ የትምህርት ቀን (በከፊል-መቅረት) ተማሪው ያልተገኘና ያመለጠው ከሆነ፤ ለዚያን ቀን ቀሪ-ሆኖ የሚመዘገብ እና ይህ-መቅረት ፈቃድ-የማግኛ ማስታወሻ እንዲያመጣ ሊያነሳሳ-የሚችል ሊሆን ይችላል።

በ'Section C.1' ከዚህ በታች - ፈቃድ-ያገኘ መቅረቶች (excused absences) በሚለው ስር - በማንኛውም-ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉት መቅረቶች (Absences)፤ ተዘርዝረዋል። ለአምስት(5) ወይም ከዚያ በላይ ተከታታይ ቀናቶች በማንኛውም-ምክንያት የሚከሰቱ መቅረቶች (Absences)፤ በ'Section C.2' ውስጥ እንደተዘረዘረው፤ ፈቃድ-ለማግኘት (excused-ለመሆን) ተጨማሪ ሰነዶችን ያስፈልጋሉ።

1. ፈቃድ-ያገኙ መቅረቶች(Excused Absences)

የሚከተሉትን መቅረቶች (absences) - ከወላጅ/አሳዳጊ ማስታወሻ ከገባ፣ ፈቃድ-ያገኘ መቅረት (excused absence)[29] ሆኖ ከግምት-ውስጥ ሊገባ የሚችለው፤ በ 'Section C.2' ውስጥ አስፈላጊ-የሆኑት ድጋፍ-ሰጪ ሰነዶች ከገቡ፤ ፈቃድ-ሊያገኝ ይችላል:

- ለተማሪ-ህመም (ለአምስት ወይም ከዚያ በላይ ተከታታይ ቀናቶች ተማሪው ለቀረበት፣ የሐኪም ማስታወሻ-ማምጣት ያስፈልጋል)፤[30]
- ወላጅ ለሆኑ ተማሪዎች የልጅ-ህመም (ለአምስት ወይም ከዚያ በላይ ተከታታይ ቀናቶች ተማሪው ለቀረበት፣ የሐኪም ማስታወሻ-ማንጣት ያስፈልጋል)፤
- ለተማሪው፤ የሕክምና ወይም የጥርስ ቀጠሮዎች፤
- በተማሪው ቤተሰብ ውስጥ ሞት ሲከሰት፤
- መባረር (Exclusion) - ከኮሎምብያ ዲስትሪክ ባለስልጣናት በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት - ባለው ተገልሎ-የመቆየት (quarantine)፣ ተላላፊ-በሽታ፣ ብክለት (infection)፣ ተወርሮ-መበከል (infestation)፣ ወይም ሌላ ከሌሎች ተማሪ በሕክምና ወይም ለጤና ምክንያቶች በሚከሰትበት ሳቢያ፤
- ተማሪው የዳኝነት-ሂደቶች (Judicial proceedings) ወይም የፍርድ-ቤት ትዕዛዝ የሚደረግ እንቅስቃሴን - በድርጊቱ አንዱ አካል በመሆን ወይም መጥሪያ-በማግኘቱ ምክንያት ማከፈል በሚያስፈልገው-ጊዜ፤
- የሃይማኖት ክብረ-በዓላትን በሚከበር ጊዜ፤

---

[29] *See* 5-A DCMR § 2102.2.

[30] የተማሪዎች፤ ህመማቸው በሆስፒታል ውስጥ መግባት የሚያስፈልግ ከሆነ ወይም ከሦስት ሳምንታት በላይ በቤት ውስጥ ሆነው-ከቆዩ - ለቤት-ውስጥ ወይም ሆስፒታል ውስጥ የትምህርት አሰጣጥ ፕሮግራም (Home and Hospital Instruction Program (HHIP) - ብቁ-ሊሆኑ ይችሉ-ይሆናል። ለተጨማሪ መረጃዎች፤ ተዛማጅ-የሆነውን የDCPS ፖሊሲን በhttps://dcps.dc.gov/service/home-and-hospital-instruction ላይ ተመልከቱ።

- የተማሪዎችን ወላጅ ወላጅ ወይም አሳዳጊ - ወዲያውኑ ወደ የውትድርና ስራቸው ከመሰማራታቸው በፊት ወይም ከተሰማሩበት በታ ሲመለሱ - ተማሪዎች - መቅረቶች (Absences) ማግኘት የሚፈቅድላቸው ሲሆን፤
- የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች ወይም ሌላ ሁኔታዎች - በDCPS ፈቃድ ሲያገኙ፤

በድንጋጌው ላይ ከተገለጸው ተጨማሪ ሆኖ እንደምክንያት ሊቀርብ-የሚችለውን፤ DCPS የሚከተሉትን ተጨማሪ-ሁኔታዎች እንደ ፈቃድ ያገኙ መቅረቶች (excused absences) አድርጎ-ይመድባቸዋል:

- ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች - ተማሪዎች የሚያደርጉት የኮሌጅ ጉብኝት (በትምህርት ዓመቱ-ውስጥ እስከ ሦስት የተጠራቀመ ቀናቶች)፤
- ከK እስከ 8ኛ ክፍሎች ላሉ ተማሪዎች - የትምህርት ቤት ጉብኝቶች (ለምሳሌ፤ የ5ኛ ክፍል ተማሪ፣ ተመዝግቦ-ለመማር ከመወሰን በፊት የመካከለኛ ደረጃ/middle ትምህርት ቤትን መጎብኘት) እስከ - ለአንድ ቀን ያህል)
- ለመውለድ-የሚጠበቁ ወይም ወላጅ-የሆኑ ተማሪዎች መቅረቶች - ለተወሰነ የጊዜ-ገደብ በሐኪማቸው በተገለጸው መሠረት መቅረቶች እና ማንኛውም በሕጉ መሰረት መሰጠት ያለበት ማመቻቻዎች፤
- ልጆቻችንን ወደ ስራ የመውሰድ-ቀን (Take Our Children to Work Day)፣ እና
- ከሃይማኖራዊ ክብረ-በዓላት ውጪ የሚከበሩ ወይም የሚደረጉ ዝግጅቶች (እስከ አምስት የተጠራቀመ ቀናት - በትምህርት ዓመቱ-ውስጥ)።

የሚከተሉትን መቅረቶች (absences)፤ ከወላጆች የጽሁፍ ሰነድ ሳይቀርብ፣ በትምህርት ቤቱ ማረጋገጫ በተሰጠው መሠረት - ፈቃድ ሊያገኝም የሚችል-ይሆናል:[31]

- በትምህርት ቤት ባለስልጣናቶች፤ ህጋዊ-የሆነ ከትምህርት-ቤት ውጪ እገዳ ወይም ማበረር፤
- በመጥፎ-የአየር ሁኔታ ምክንያት፣ በይፋዊ እንቅስቃሴዎች፣ በክብረ-በዓላት፣ የማይሰሩ-የህንፃ መሣሪያዎች ሲኖሩ፣ ደህንነቱ-ያልተጠበቀ እና ንጽህና-የጎደለው ሁኔታ ሲኖር፣ ወይም ሌላ ሁኔታ(ዎች) ወይም የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች የክፍለ-ጊዜ እገዳዎችን በሚጠይቁ-ጊዜ፤ የትምህርት ክፍለ-ጊዜውን በጊዜያዊነት ማገድ፣ እና
- የኮሎምብያ ዲስትሪክት ባለው ሕጋዊ የመጓጓዣ ለተማሪዎች ማቅረብ ኃላፊነቱን ለመወጣት የማይችልበት፤ የኮሎምብያ ዲስትሪክት መጓጓዣ ለተማሪዎች ማቅረብ ሳይችል-ሲቀር።

ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ፈቃድ-ያገኙ መቅረቶች (excused absences) ውስጥ ያልተሸፈኑ - መቅረት እንደሚኖር ተማሪው ወይም ወላጅ ይኖራል-ብለው የሚገምቱ ከሆነ፣ ወይም ከተወሰነ ሁኔታ ወይም ክስተት ጋር ግንኙነት ያለው ቀጣይነት ያለው መቅረት እንደሚከሰት ከጠበቁ፤ ወደ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር - በልዩ ሁኔታ ሊከሰት የሚችል ፈቃድ-ያገኘ መቅረት ( excused absence)ን ሊያስገቡ-ይችላሉ። ርዕሰ-መምህሩ፣ ከመፍቀዱ-አስቀድሞ፤ ከእርሱ ወይም ከእርሷ የትምህርት አሰጣጥ ጠቃላይ-ስራ አስኪያጅ ጋር - ፈቃድ ያገኘ የመቅረት (excused absence) ጥያቄውን - ውሳኔውን-ሰጥቶ መፍቀድ-እዳለበትና እንደሌለበት ማማከር አለበት። ማንኛውም መቅረት - ፈቃድ-ያገኘው መቅረት (excused absence)ን መስፈርት-ያላሟላ፣ ወይም ፈቃድ-ያገኘው መቅረት (excused absence)ን ለመደገፍ የሚያስችል አስፈላጊ-የሆኑ ሰነዶችን በተፈቀደው የጊዜ-ገደብ ውስጥ ማቅረብ ካልቻለ፤ መቅረቱ - ፈቃድ-ያላገኘ መቅረት (unexcused absence) ተብሎ ይመደባል።

2. አስፈላጊ-የሆኑ ሰነዶች

የወላጅ ወይም የአሳዳጊ የጽሁፍ ማስታወሻ፤ እስከ **አራት (4) ቀን ተከታታይ ቀናቶች**[32] ማንኛውም መቅረት - በቂ ሰነድ-ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። ማንኛውም እንደዚህ ዓይነት መቅረት - ከላይ በማስታወሻው ላይ እንደምክንያት በተሰጡት ፈቃድ-ያገኘ

---

[31] *See* 5-A DCMR § 2102.2.

[32] DCPS፣ የቀለም-ትምህርት የቀን-መቁጠሪያውን በአራት ተርሞች ይከፍላል፤ ይህም የውጤት-አሰጣጥ ወቅቶች (grading periods) ተብሎ፣ ወይም አድቫይዘሪ ፒሬድስ (advisory periods) ተብሎ-የሚታወቅ ሲሆን፤ እያንዳንዱ እኩል-የሆኑ በሚባል-ቁጥር ባላቸው የትምህርት ቀናትን የያዙ-ናቸው። በአንድ-ሴሚስተር (semester) ውስጥ - ሁለት ተርሞች (terms)፣ አሉ።

መቅረት (excused absence) ስር የሚመደብ ከሆነ፤ ፈቃድ-ማግኘት ይችላል።

ተማሪው ለ**አምስት (5) ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ተከታታይ ቀናቶች** - ከቀረ፤ በሚከተሉት-መሠረት - ከግንኙነቶች ባለፈ ሁኔታ ለመቅረቱ ፈቃድ-እንዲያገኝ ለማድረግ - ተጨማሪ ሰነድ ያስፈልገዋል:

- በሕክምና ወይም የጥርስ-ቀጠሮ፤ መቅረቶች (absences): የተማሪውን መቅረት የሚገልጽ፤ ከሐኪሙ ወይም በድርጅቱ ውስጥ ከሚሰራ ሠራተኛ በሐኪሙ/የጥርስ-ሃኪሙ የቢሮው የራስጌ የደብዳቤ መፃፊያ ወረቀት (letterhead) ባለው ላይ የተፃፈ እና በተገቢው የቢሮው ሹም የተፈረመ የጽሁፍ-መግለጫ መግባት አለበት፤
- የዳኝነት-ሂደቶች (Judicial proceedings): የተማሪውን በዳኝነት-ሂደቶች (judicial proceedings) ላይ መገኘት እንደሚያስፈልገው የሚገልጽ ሰነድ - ከፍርድ-ቤቱ፣ የተማሪውን በሁሉን ተገቢ-በሆኑ ቀናቶች መገኘት-እንዳለበት የሚገልጽ ሰነድ መቅረብ አለበት፤ እና
- በተማሪው የቅርብ-ቤተሰብ ውስጥ፣ ሞት ሲከሰት: የቀብር ፕሮግራሞች፤ እንደ ተገቢ-የሆኑ ሰነዶች አቀራረብ ሁኔታ፤ ተቀባይነት ሊኖረው ይችል-ይሆናል።

a. የመለየት (Isolation) እና ተገልሎ-የመቆየት (Quarantine) ሰነዶች፤ የማስፈለጋቸው - መስፈርቶች

ለCOVID-19 - ቫይረሱ እንዳለባቸው በምርመራ ስለታወቀ (positive ስለሆኑ፤ ተለይተው-መቆየት (isolate) ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች፤ ወላጅ ወይም አሳዳጊው፤ የጽሁፍ የመለየትና የመቆየት (isolation) ሰነድን ማቅረብ አለባቸው። የጽሁፍ ማስታወሻው፤ ለCOVID-19 የተጋለጡበትን ቀን ያካተተ እና የCOVID-19 ምርመራ-ውጤቱ ቫይረሱ እንዳለ (positive) እንደሆነ የሚያሳይ የምርመራ ማረጋገጫን ማካተት አለበት። ተገልሎ-መቆየት (quarantine) እና ራስን-መለየት (isolation) በተመለከተ፣ ተያያዥ የሆኑ ተጨማሪ መስፈርቶች፤ በ'Appendix B' ውስጥ ቀርቧል።

### D. የክትባት/Immunization እና በትምህርት-ገበታ የመገኘት (Attendance) መስፈርቶች

በኮሎምብያ ዲስትሪክት ትምህርት ቤት ውስጥ ለመማር፤ የሕዝብ፣ የግል፣ የቤተክርስቲያን፣ እና ገለልተኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥን ጨምሮ ለመማር፤ ተማሪው በዲሲ ጤና (DC Health) መስፈርቶች ውስጥ ተገዢ-መሆንና ክትባት-የወሰደ መሆን አለበት።[33,34] DCPS የክትባት መስፈቶችን አያዘጋጅም፤ ነገር ግን ሁሉም ተማሪዎች ከእነዚህ መስፈርቶች ጋር ተገዢ-እንደሆኑ ማረጋገጥ-አለበት። የዲሲ ሕግ፤ ውሱን-በሆኑ ክስተቶች ስር - የተማሪ የክትባት መስፈርቶችን - በሕክምና ወይም በሃይማኖት ምክንያት እንዲነሳ-ለማድረግ (exemptions)፤ ሊፈቅድ-ይችላል።[35]

የተማሪው የሕክምና መዝገብ - ለሕግ-ተገዢነትን የማያሳይ ከሆነ፤ ወይም በሕክምና ወይም በሃይማኖት እንዲነሳ-የሚያደርግ (exemptions) በሰነድነት-ከሌለ፤ ትምህርት ቤቱ ወዲያውኑ - ለወላጅ/አሳዳጊ ወይም ለአዋቂ-ተማሪው፤ የክትባት(ቶች) መረጃ እንደሌለ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት። ተማሪው በ20-የትምህርት ቀን ገደብ ውስጥ - ለሕጉ-ተገዢነቱን ለማሳየት ካላመጣ፤ ወላጅ/አሳዳጊ አስፈላጊ-የሆነውን ሰነድ እስከሚያመጡ ድረስ - ትምህርት ቤቱ፣ ተማሪው ከትምህርት ቤት እንዲወገድ ያደርጋል። ይህን-ዓይነቱ መወገድ - ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረት (unexcused absence) ተብሎ-

---

[33] እባካችሁ፤ ስለ ክትባት (immunization) መረጃዎች፤ የዲሲ ጤና (DC Health)ን ገጽ፤ በ https://dchealth.dc.gov/page/immunizations ላይ ጎብኙ።

[34] *See* D.C. Official Code § 38-503; 5-E DCMR § 5300.1, *et seq.* ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፣ እባካችሁ - የ'DC Office of the State Superintendent of Education (OSSE)'ን No Shots, No School! ጎብኙ።የኮሎምብያ ዲስትሪክት የክትባት ፖሊሲ (District of Columbia Immunization Policy) ለበአካል-ተገኝቶ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (Attendance) ድህረ-ገጹ፣ በ http://bit.ly/NoShotsNoSchool ላይ ይገኛል።

[35] ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፣ እባክዎን http://bit.ly/NoShotsNoSchool ይጎብኙ።

የሚወሰድ፣ እና በ‘ Attendance Protocol’ ላይ በSections F.5 እና በF.6 ላይ በሚገኘው በዚህ-ፖሊሲ ላይ በተዘረዘረው-መሠረት፣ ጣልቃ-ገብነቶች እንዲደረጉ ሊያስፈልግ-ይችላል።

## E. በትምህርት ቤት ስፖንሰር-በሆኑ እንቅስቃሴዎች ምክንያት፤ የሚደረጉ መቅረቶች (Absences)

1. አትሌቲክስ (Athletics)

በመደበኛ የትምህርት ክፍለ-ጊዜ ሰዓታት ውስጥ በሚካሄዱ በDCPS-ስፖንሰር በተደረገ የአትሌቲክ ዝግጅቶች ላይ ተማሪዎች በሚካፈሉበት-ጊዜ፤ እንደ ‘የተገኙ/present’ ሆኖ ይወሰድላቸዋል። ተማሪዎች በሁሉም በትምህርት-ገበታ የመገኘት (attendance) መስፈርቶች ላይ - በስቴት ድንጋጌዎች እና በDCPS ፖሊሲ ላይ በተጠቆመው-መሠረት፤ እንዲከተሉ - ይጠበቅባቸዋል። በማንኛውም ልምምድ ውስጥ ለመካፈል፣ ማንኛውም አትሌቲክስ ሙከራ፣ ልምምድ፣ ጨዋታ፣ ወይም ውድድር ለመሳተፍ፤ ተማሪው በትምህርት ቀኑ ላይ - ፈቃድ-ያገኘ መቅረት (excused absence) እስከሌለው ድረስ፤ ወደ ትምህርት ቤት ከዝግጅቱ-በፊት መገኘት አለበት።[36] በህክምና-ሁኔታ ብቁነትን ያገኙ በርቀት (virtual) የትምህርት-አሰጣጥ ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎች፤  በአካል-ተገኝቶ (in-person) እንቅስቃሴዎች እና አትሌቲክስ ውስጥ ለመሳተፍ ብቁ-አይሆኑም። በተመሣሣይነት፤ ተገልሎ-በመቆየት (quarantine በማድረግ) ምክንያት፤ ተማሪው ከቀረ፤ ለበአካል-ተገኝቶ (in-person) እንቅስቃሴዎች እና አትሌቲክስ ብቁ-መሆን አይችልም።

2. ሌላ እንቅስቃሴዎች

በDCPS-ስፖንሰር በተደረጉ ዝግጅቶች፣ በመስክ-ጉዞዎች ውስጥ የሚሳተፉ፣ ወይም በመደበኛ የትምህርት ቀኑ ወቅት ወደ ውጪ-ሃገር ለትምህርት የተጓዙ ተማሪዎች፤ በትምህርት-ገበታ የተገኙ/present ሆነው-ይወሰዳሉ።

3. የግል የትምህርት ፕሮግራም (Individualized Education Program (IEP) ወይም የ‘504 Plan’ አገልግሎት - አሰጣጥ

በ‘IEPs’ ወይም በ‘504 plans’ ላይ በሰነድነት በተቀመጠው - ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶችን ለማግኘት ክፍለ-ጊዜው ውስጥ ያልተገኙ ተማሪዎች፤ በትምህርት-ገበታ የተገኙ/present ሆነው-ይወሰዳሉ።

4. እገዳዎች (Suspensions)

በትምህርት ቤት እገዳዎች (suspensions) ውስጥ እያሉ፤ ተማሪዎች - የተገኙ/present - ሆነው-ምልክት መደረግ አለበት። ከትምህርት ቤት-ውጪ በሆነ እገዳዎች (out-of-school suspensions) ምክንያት የቀሩ-ተማሪዎች፤ ፈቃድ-ያገኘ መቅረት ውስጥ ይመደበባሉ።

## F. ከመቅረቶች ጋር ተዛማጅ-የሆነ፤ በትምህርት ቤት መሠረት ያደረገ በትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘትና አለመገኘት ጣልቃ-ገብነቶች (School-Based Attendance Interventions)

1. ከK-2 ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ፣ ተማሪዎች

የሚከተሉትን - በትምህርት ቤት ላይ መሠረት ያደረገ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘትና-አለመገኘት ጣልቃ-ገብነቶችን (school-based attendance interventions) - ከመቅረቶች ጋር ግንኙነት-ባለው ሁኔታ፣ ከK-12 ክፍሎች ውስጥ ላሉ  - የርቀት (virtual) ትምህርት-አሰጣጥን የሚያገኙትን ጨምሮ፤ ለሁሉም ተማሪዎች በስራ-ላይ ይውላል:

[36] 5-F DCMR § 104.8.

| የጊዜ አቀማመጥ (Timeline) | የትምህርት ቤት ኃላፊነቶች |
|---|---|
| **እያንዳንዱ ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረት/unexcused absence (ሙሉ ወይም በከፊል መቅረቶች/absences)** | **ሮቦ-ኮል (Robo-call)** (ከ'Blackboard' የተላከ) በእያንዳንዱ ምሽት-ላይ፣ ተማሪው አንድ ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረት (unexcused absence) እንዳለው-ለቤተሰብ ለመንገር የተላከ-ነው። |
| **3 የተጠራቀመ (cumulative) በከፊል ወይም የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)** | AC/AD፤ ከአስፐን (Aspen) ላይ፤ የ**3-ቀን ዓለም-ዓቀፍ የመቅረት (Universal Absence) ደብዳቤን** ለወላጆች ይልካል።<br><br>ለርቀት (virtual) ተማሪዎች ብቻ፤ AC/AD፣ የደህንነት-ሁኔታን ለማረጋገጥ (**wellness check**) ወደ ተማሪው መኖሪያ-ቤት የስልክ-ጥሪ ያደርጋል። የደህንነት-ሁኔታን ማረጋገጫው (wellness check) ማካተት ያለበት፤ ስለ ተማሪው በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (attendance) ሁኔታ መወያየት - የቴክኖሎጂ ወይም ሌላ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች ካሉ መለየትን እና ማንኛውም አስቸጋሪ ሁኔታዎች-ካሉ እና አስፈላጊ የሆኑ የመረጃ-ምንጮች ለተማሪው-ስኬታማ-መሆን ያስፈልጉ-እንደሆነ ጨምሮ ይወያያሉ። |
| **4 የተጠራቀመ (cumulative) የከፊል ወይም የሙሉ-ቀን መቅረቶች/absences (ፈቃድ-ያገኘ ወይም ያላገኘ/excused or unexcused)** | የተማሪውን በትምህርት-ገበታ መገኘት ሁኔታ ለመወያየት፣ **አስተማሪው ወደ ተማሪው መኖሪያ-ቤት፣ ስልክ-ጥሪ ያደርጋሉ**። |
| **5 የተጠራቀመ (cumulative) በከፊል ወይም የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)** | AC/ADው፤ '**5-Day Universal Absence Letter**'ን ከአስፐን (Aspen) ላይ ወደ ተማሪው መኖሪያ-ቤት - የተማሪ በትምህርት ገበታ-ላይ የመገኘት ኮንፈረንስ (Student Attendance Conference (SAC) እንደሚካሄድ ለወላጅ/አሳዳጊ ለማሳወቅ ይልካል።[37] |
| **5 የተጠራቀመ (cumulative) የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)** | AC/ADው፤ የመቅረቱን ከስር-መሠረት ያለውን ችግር በሰነድነት ለማስቀመጥ እና ለመወሰን፣ እና አስፈላጊ የሆኑ ጣልቃ-ገብነቶችን ለመስጠት እና በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት የእርምጃ ዕቅድ (Attendance Action Plan)ን ለመቅረጽ፤ መምራቱ(referral)-በተደረገ በ5 ቀናቶች ውስጥ፣ **'SAC' ን ከወላጅ ጋር** እና ከተማሪው ጋር፣ ተገቢ-ከሆነ፤ ያካሂዳል። ይህን ስብሰባ - በአስፐን (Aspen) ላይ፣ 'AC/AD'ው በሰነድነት-ያስቀምጣል። ተማሪው - 'IEP' ካለው፤ AC/ADው - የአካባቢውን የትምህርት ድርጅት ወኪል ተጠሪ (local education agency representative designee (LEARD)ን እና ጉዳይ አስፈፃሚውን ማሳወቅ አለበት።<br><br>ሣምታዊ-በሆነ አሠራር መሠረት፤ ወደ 5-ቀን ፈቃድ ያላገኘ በትምህርት ገበታ-ላይ ያለመገኘት (unexcused absence) የገደብ-ደረጃ/threshold ላይ የደረሱትን ሁሉንም ተማሪዎች ዝርዝር፤ የ'SAC' ስብሰባ በተደረገ-ጊዜ እንቅፋት-ናቸው ተብለው ማጠቃለያ ከተሰጠው ሪፖርት ጋር አድርጎ - AC/ADው ለ'MTSS Leadership Team' - ያቀርባል።<br><br>**ወደ 5-ቀን ፈቃድ ያላገኘ በትምህርት ገበታ-ላይ ያለመገኘት (unexcused absence) የገደብ-ደረጃ/threshold ላይ የደረሱ ተማሪዎች፤ የበለጠ ዒላማ-ያደረገ (targeted) እርዳታዎች ያስፈልጓቸው እንደሆነና እንዳልሆነ ከግምት-ውስጥ ለማስገባት -** |

[37] *See* 5-A DCMR § 2103.4

| | |
|---|---|
| | **በ‘MTSS Leadership Team’ ምልከታ-ይደረግባቸዋል።** የ‘Tier II’ ወይም ‘III’ መመራት/referral - ለማንኛውም ተማሪ የሚያስፈልግ ከሆነ፤ ይህ መመራት/referral፣ በMTSS system መደረግ ያለበት እና በትምህርት ቤት-መሠረት ያደረገ (school-based) የ‘MTSS’ ጣልቃ-ገብነት የግንኙነት ሠራተኛው (intervention POC) - ‘AC/AD’ውን በማግኘት - በስራ-ውሎ የሚገኘው የ‘SAC documents’ን ለማግኘት ያነጋግራሉ።[38] |
| **7 የተጠራቀመ (cumulative) የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)** | AC/AD፤ **ሜትሮፖሊታን ፖሊስ መምሪያ (Metropolitan Police Department (MPD) - የማስጠንቀቂያ-ደብዳቤን፣** አስፐን (Aspen) በመጠቀም፤ ለወላጆች ይልካል። |
| **10 የተጠራቀመ (cumulative) በከፊል ወይም የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)**<br>______________________<br>**10 የተጠራቀመ (cumulative) የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያገኘ መቅረቶች (excused absences)** | AC/AD፤ ከአስፐን (Aspen) ላይ፤ የ**10-ቀን ዓለም-ዓቀፍ የመቅረት (Universal Absence) ደብዳቤን** ለወላጅ ይልካል።<br><br>**የ‘MTSS Leadership Team’፤ የሁሉንም ተማሪዎች (ዕድሜያቸው ከ5-17 የሆኑ) እስከ- 10-ቀን ፈቃድ ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች (unexcused absence) ገደብ/threshold ላይ የደረሱ ዝርዝሮችን ለመመልከት እና**፤ ሌላ ተጨማሪ ዒላማ ያደረገ እርዳታ-እንደሚያስፈልግና እንደማያስፈል ከግምት-ውስጥ ያስገባል። የ‘Tier II’ ወይም ‘III’ መመራት/referral - ለማንኛውም ተማሪ የሚያስፈልግ ከሆነ፤ ይህ መመራት/referral፣ በMTSS system መደረግ ያለበት እና በትምህርት ቤት-መሠረት ያደረገ (school-based) የ‘MTSS’ ጣልቃ-ገብነት የግንኙነት ሠራተኛው (intervention POC) - ‘AC/AD’ውን በማግኘት - በስራ-ውሎ የሚገኘው የ‘SAC documents’ን ለማግኘት ያነጋግራሉ።<br>______________________<br>ዕድሜያቸው ከ5 – 13 ለሆኑ-ብቻ፣ የሚሆን መሆኑን-አስታውሱ: ሁሉም በትምህርት ገበታ የመገኘት ጣልቃ-ገብነቶች (attendance interventions) ተፈፃሚ-እንዲሆኑ ከተደረገ እና በሰነድነት በአስፐን (Aspen) ውስጥ ከተቀመጠ፤ AC/ADው፣ ለትምህርታዊ ቸልተኝነት፤ **ተማሪውን ወደ ‘CFSA’ ይመራዋል**። |
| **15 የተጠራቀመ (cumulative) - በከፊል ወይም የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)**<br>______________________<br>**15 የተጠራቀመ/cumulative የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)** | AC/AD፤ ከአስፐን (Aspen) ላይ፤ የ**15-ቀን ዓለም-ዓቀፍ የመቅረት (Universal Absence) ደብዳቤን** ለወላጆች ይልካል።<br>______________________<br>ዕድሜያቸው ከ14 – 17 ለሆኑ-ብቻ፣ የሚሆን መሆኑን-አስታውሱ: ሁሉም ጣልቃ-ገብነቶች ሁሉም ፈቃድ-ካገኙ እና በሰነድነት በአስፐን (Aspen) ውስጥ ከተያዙ፤ AC/ADው፣ ከትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘት ባለሞያተኛ ጋር በቅንጅት በመሆን፣ **ተማሪውን/ቤተሰቡን ወደ ማህበራዊ አገልግሎቶች ፍርድ-ቤት** ክፍል እና ለጠቃላይ አቃቤ-ሕግ ቢሮ መምራት (refer) ማድረግ አለበት። |
| **20 *<u>የተጠራቀመ (consecutive)</u>* የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ** | AC/ADው፤ የ‘**initial withdrawal letter**’ን - ለወላጅ ይልክ እና፣ ለወላጅ/አሳዳጊ የተማሪውን ከትምህርት ቤት ለመልቀቅ ብቁነቱን ለማሳወቅ፤ **ወደ ተማሪው መኖሪያ ቤት የስልክ-ጥሪ** ያደርጋል። |

[38] ጉዳተኝነት ሊኖረው ይችላል ተብሎ የሚጠረጠረውን ተማሪ፤ የመጀመሪያ (initial) ግምገማ ለማዘግየት - ‘MTSS’ ጥቅም-ላይ ሊውል አይችልም። ከጉዳተኝነት ግአር የሚገኝ ልጅ ነው ለተባለ ተማሪ - በሚያስፈልጉት በልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ላይ፤ DCPS ሁልጊዜ፣ የልዩ ትምህርት (special education) መምራት/referralን እና የመጀመሪያ (initial) ግምገማ እንዲደረግ ማነሳሳት አለበት።

| | |
|---|---|
| **መቅረቶች (unexcused absences)**[39] | AC/ADው፤ ሁሉንም የማግኛ-ጥረቶችን ካጠናቀቀ በኋላ፤ የ'**final withdrawal letter**'ን - ለወላጅ በመላክ፤ የወላጅን ለመልቀቅ (withdraw ለማድረግ) ያለውን-ፍላጎት ለማሰወቅም-ሲባል፣ መላክ-አለበት። ትምህርት ቤቱ፤ መልቀቂያውን ከመስጠቱ በፊት፤ ሁሉንም አስፈላጊ የሆኑትን የጣልቃ-ገብነቶች እርምጃዎች ማከናወን *ኣለበት*፤ እና ትምህርት ቤቱ ሁሉንም ሰነዶች በአስፐን (Aspen) ላይ መመዝገብ ያለበት እና፣ ከርዕሰ-መምህሩ እና የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጁ ማጽደቂያ-ፈቃድ ማግኘት አለበት። በልዩ ትምህርት አገልግሎቶች አማካኝነት 'IEP' የሚያገኙ ተማሪዎች፤ ትምህርት ቤቱ ወላጅን ለማግኘት ተጨማሪ ተገቢ-የሆኑ ወላጅን-የማነጋገር ጥረቶችን - እንዳደረገ ሳያሳይ - ሊለቀቁ (withdrawn ሊደረጉ) የማይችሉ እና፣ ከDCPS የልዩ ትምህርት-አሰጣጥ (DCPS Division of Specialized Instruction) ፈቃድ-ሳያገኝ መልቀቅ-አይችሉም። |

2. በPre-K ውስጥ የሚገኙ፣ ተማሪዎች

የPre-K ተማሪዎች፤ ስለ ፈቃድ-ያላገኘ እና ፈቃድ ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች - ልክ እንደ ከK-12ኛ ክፍል-ተማሪዎች ሁሉ በአንድ-ዓይነት በሆነ ሁኔታ ላሉት መስፈርቶች ተገዢ-ይሆናሉ። ምንም-እንኳን - ወደ 'CFSA'፣ በትምህርት-ገበታ ላይ በመገኘትና-ባለመገኘት ላይ መሠረት ያደረገ መምራት - (attendance-based referrals) - ዕድሜያቸው ከአምስት (5) ዓመትበታች ለሆኑ ተማሪዎች ባያስፈልግም፤ ትምህርት ቤቶች፣ በትምህርት ቤት ላይ መሠረት ያደረገ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘትና-አለመገኘት ጣልቃ-ገብነቶችን (school-based attendance interventions)፣ ከዚህ-በታች በተገለጸው መሠረት - ያስፈጽማሉ።[40]

የሚከተሉትን - በትምህርት ቤት ላይ መሠረት ያደረገ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘትና-አለመገኘት ጣልቃ-ገብነቶችን (school-based attendance interventions) - ከመቅረቶች ጋር ግንኙነት-ባለው ሁኔታ፣ ለPre-K ተማሪዎች - በሁሉ የመማሪያ ሞጁሎች ውስጥ በስራ-ላይ ይውላል:

| የጊዜ አቀማመጥ (Timeline) | የትምህርት ቤት ኃላፊነቶች |
|---|---|
| **እያንዳንዱ ፈቃድ-ያላገኘ (Each unexcused) በከፊል ወይም የሙሉ-ቀን መቅረቶች (absences)** | **ሮቦ-ኮል (Robo-call)** (ከ'Blackboard' የተላከ) በእያንዳንዱ-ቀን ምሽት-ላይ፣ ተማሪው አንድ ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረት (unexcused absence) እንዳለው-ለቤተሰብ ለመንገር የተላከ-ነው። |
| **3 የተጠራቀመ (cumulative) በከፊል ወይም የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)** | AC/AD፤ ከአስፐን (Aspen) ላይ፤ የ**3-ቀን ዓለም-ዓቀፍ የመቅረት (Universal Absence) ደብዳቤን** ለወላጆች ይልካል። |
| **4 የተጠራቀመ (cumulative) የከፊል ወይም የሙሉ-ቀን መቅረቶች/absences (ፈቃድ-ያገኘ ወይም ያላገኘ/excused or unexcused)** | የተማሪውን በትምህርት-ገበታ መገኘት-ሁኔታ ላይ ለመወያየት፣ **አስተማሪው ወደ ተማሪው መኖሪያ-ቤት፣ ስልክ-ጥሪ ያደርጋሉ።** |
| **5 የተጠራቀመ (cumulative) በከፊል ወይም የሙሉ-ቀን** | AC/ADው፤ '**5-Day Universal Absence Letter**' ከአስፐን (Aspen) ላይ ወደ ተማሪው መኖሪያ-ቤት - የተማሪ በትምህርት ገበታ-ላይ የመገኘት ኮንፈረንስ (Student Attendance Conference (SAC) እንደሚካሄድ ለወላጅ/አሳዳጊ ለማሳወቅ ይልካል። |

[39] *See* D.C. Official Code § 38-236.04(c).
[40] የPre-K ተማሪዎች - በትምህርት ቤት የመገኛ አስገዳጅ-የሆነ እድሜ ባለመሆኑ ምክንያት፤ የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)ን - 'CFSA'ን በማነጋገር፣ ትምህርት ቤቶች ሪፖርት ማድረግ አይችሉም።

| | |
|---|---|
| **ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)**<br><br>**5 የተጠራቀመ (cumulative) የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)** | AC/ADው፤ የመቅረቱን ከስር-መሠረት ያለውን ችግር በሰነድነት ለማስቀመጥ እና ለመወሰን፣ እና አስፈላጊ የሆኑ ጣልቃ-ገብነቶችን ለመስጠት እና በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት የእርምጃ ዕቅድ (Attendance Action Plan)ን ለመቅረጽ፤ **'SAC' ን ከወላጅ ጋር** ያካሂዳል። ይህን ስብሰባ - በአስፐን (Aspen) ላይ፣ 'AC/AD'ው በሰነድነት-ያስቀምጣል። የ'Early Childhood Education (ECE) Family Service' የእርዳታ ቡድን (Title 1 schools)ን - ለሚያገኙ ትምህርት ቤቶች፤ ወደ 'ECE Family Services' ቡድኑ፤ መምራት (referral) - መደረግ-አለበት።<br><br>'AC/AD' እና 'SAC' - ቤተሰቡን - በስልክ-ጥሪዎች፣ በቴክስቶች (texts)፣ እና በኢሜሎች ማግኘት ካልቻለ፤ በአስቸኳይ-ጊዜ ተጠሪ የሆነውን አድራሻዎች እና ሌሎች የሚታወቁ አድራሻዎችን ማነጋገር አለባቸው። ምንም ዓይነት ግንኙነት ማድረግ ካልተቻለ ወይም የተማሪውን ጤናማና ደህንነት ለማረጋገጥ ካልተቻለ፤ ቡድኑ፣ ከ'ECE' ቡድን ጋር መማከር እና ለ'CFSA' መምራት (referral) ማድረግ ማስፈለግና አለማስፈለጉን መወያየት-አለበት። |
| **10 የተጠራቀመ ቀናት (cumulative days) - መቅረቶች/absences**<br><br>**10 የተጠራቀመ/cumulative የሙሉ-ቀን፣ መቅረቶች/absences** | AC/ADው፤ **'10-Day Universal Absence Letter'** ከአስፐን (Aspen) ላይ ወደ ተማሪው መኖሪያ-ቤት ይልካል።<br><br>ዕድሜያቸው ከ5 – 13 ለሆኑ-ብቻ፣ የሚሆን መሆኑን-አስታውሱ: ሁሉም በትምህርት ገበታ የመገኘት ጣልቃ-ገብነቶች (attendance interventions) ተፈፃሚ-እንዲሆኑ ከተደረገ እና በሰነድነት በአስፐን (Aspen) ውስጥ ከተቀመጠ፤ AC/ADው፣ ለትምህርታዊ ችልተኝነት፤ **ተማሪውን ወደ 'CFSA' ይመራዋል**። |
| **20 የተጠራቀመ (cumulative) የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)**[41] | AC/ADው፤ የ**'wellness check'** በስልክ-ጥሪዎች፣ በቴክስቶች (texts) እና ኢሜሎች አማካኝነት ለማጠናቀቅ፤ የተማሪውን ወላጅ ያነጋግራል። **የደህንነት-ሁኔታን ማረጋገጫው (wellness check) የሚያካትተው**፤ ስለ ተማሪው በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (attendance) ሁኔታ መወያየት - የቴክኖሎጂ ወይም ሌላ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች ካሉ መለየትን እና ማንኛውም አስቸጋሪ ሁኔታዎች-ካሉ እና አስፈላጊ የሆኑ የመረጃ-ምንጮች ለተማሪው-ስኬታማ-መሆን ያስፈልጉ-እንደሆነ ጨምሮ ውይይቶችን ያካትታል።<br><br>AC/ADው፤ የአስቸኳይ-ጊዜ ተጠሪዎችን እና ሌሎች የታወቁ በመገኛ-ዝርዝር ውስጥ የሚገኙትን ያነጋግሯሉ፤ እና ከ'Central Services Attendance' ባለሞያተኛ ጋር እና ከ'Early Childhood Education Division' ጋር፤ **የመልቀቅ ውሳኔ (withdrawal determination)ን** ከመወሰን-አስቀድሞ ማማከር ያስፈልገዋል።<br><br>የPre-K ተማሪዎች ሊያደርጉ የሚችሉት፤ ነገር ግን በመስፈርትነት የተቀመጠላቸው ያልሆነው፤ ተማሪዎ 20 የሙሉ የትምህርት ቀን ተከታታይ የሆነ ፈቃድ ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences) ከሌለው በስተቀረ፣ ፈቃድ-ባላገኘ መቅረቶች (unexcused absences) ምክንያት - ገብቶ-እንዳይማር ሊደረግ የማይችል እና ትምህርት ቤቱ የሚከተሉትን ማድረግ አለበት:<br>• ሁሉንም ቤተሰብን ለማግኘት የተደረጉ ጥረቶችን እና የተሰጡትን የእርዳታ አገልግሎቶች በሰነድነት-መያዝ፤<br>• ከሁሉም የልዩ ትምህርት (special education) ማስታወቂያ መስፈርቶች ጋር፣ ተገዢ-መሆን፤ እና<br>• ከ'Central Services Early Childhood Education Division' - ፈቃድ-የተሰጠበትን ማግኘት።<br><br>ማንም ከPre-K ተማሪ የሆነ፤ ዘግይቶ ወደ ትምህርት ቤት በመድረስ ምክንያት፤ ገብቶ-እንዳይማር ሊደረግ አይችልም። |

[41] *See* D.C. Official Code § 38-236.04(c).

### G. በተደጋጋሚ-ከመቅረት (Absenteeism) ጋር ተዛማጅ-የሆኑ፣ የተከለከሉ እርምጃዎች

የዲሲ ሕግ፤ በተለዩ እርምጃዎች - ከተማሪው መቅረት (truancy) እና በተደጋጋሚ-ከመቅረት (absenteeism) ጋር ግንኙነት በሚኖረው ጊዜ፤ የሚከተሉትን ይከለክላል:

- ማንም-ተማሪ፤ ከ18 ዓመት በላይ ካልሆነ በስተቀረ፤ በትምህርት ቤት ውስጥ ከግማሽ-በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች ከ18 ዓመት ዕድሜ በላይ በሆኑበት ትምህርት ቤት ውስጥ፤ ለመባረር (expelled) ወይም ለከትምህርት ቤት ውጪ ለሆነ እገዳ (out-of-school suspension) ወይም ለዲሲፕሊን በትምህርት-ቤት ገብቶ ላለመማር ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች ወይም አርፍዶ ወደ ትምህርት ቤት ለመድረስ ሊዳረጉ-ይችላሉ።[42]
- ተማሪው የተጠራቀመ ከ20 ወይም ከዚያ በላይ ተከታታይ የሙሉ የትምህርት-ቀም ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች (unexcused absences) ከሌለው በስተቀረ እና ትምህርት ቤቱ ሁሉንም የሚፈለጉትን እርምጃዎች መውሰዱን እና የተማሪዎችን ቤተሰብ ማነጋገሩን በሰነድነት ካልያዘ በስተቀር፤ በተደጋጋሚ በመቅረት (absenteeism) ምክንያት ምንም-ተማሪ ገብቶ-እንዳይማር ሊደረግ-አይችልም።[43]
- ከክልል ውጪ (Out-of-Boundary) ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ጨምሮ፤ ምንም ተማሪ ከትምህርት ቤቱ በተደጋጋሚ-በመቅረት (absenteeism) ከትምህርት-ቤቱ እንዲዛወር ሊደረግ አይችልም።[44] ተማሪው፤ ገብቶ-እንዳይማር የሚደረግበት ብቸኛ ምክንያት ሊሆን የሚችለው፤ የተጠራቀመ ከ20 ቀን በላይ *በተከታታይነት* ሙሉ-ከትምህርት ቀን ፈቃድ-ሳያገኝ መቅረቶች (unexcused absences) ካሉት ነው።[45]
- ማንም ተማሪ፣ በትምህርት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ እንዲለቅ (withdrawn) እንዲያደርግ የሚደረግበት ነገር አይኖርም፤ ይልቁኑ-ይህ ሊሆን የሚችለው ቢያንድ በአንድ (1) ቀን - በመጀመሪያ የትምህርት ሦስት(3) ሣምንታት ውስጥ ማስታወቂያ-ሳይሰጥ - እንደ መቅረት (absence) ወይም ወደ ሌላ የትምህርት ተቋም መዛወሩን ያሉ ማስታወቂያዎችን ሳይገልጽ፤ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት ካልቻለ-ነው። ትምህርት ቤቶች፤ "ካለምንም-ምክንያት አለመምጣት/no show" ፕሮቶኮሎችን፤ ማንኛውም ተማሪ እንዲለቅ-ከማድረግ (withdrawing) በፊት ማሟላት አለባቸው። "ካለምንም-ምክንያት አለመምጣት/no show ፕሮቶኮሎች"፤ ሂደቱ ሊከናወን የሚችለው፣ ተማሪዎች በሚማሩበት ጊዜ ከትምህርት ቤት እንዲልቅቁ (withdrawn) በሚደረጉ ጊዜ ሲሆን፣ ነገር ግን ምዝገባ-ካላደረጉ አይከናወንም።

### H. በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘትና አለመገኘት (Attendance)፣ የደረጃ-አሰጣጥ፣ እና ወደ ሌላ ክፍል-መሸጋገር

የተማሪ የደረጃ-አሰጣጥ እና ከክፍል-ወደ ክፍል ማለፍ - በሚከተሉት የተጠራቀመ ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች (unexcused absences) ምክንያት ተጽዕኖ ሊገጥመው ይችላል:

- በማንኛውም-ክፍል ውስጥ የሚገኙ ከአስር (10) ፈቃድ ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences) ያላቸው የሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎች፤ የ"FA" (በመቅረት ምክንያት የወደቀ/failure due to absences) የሚለውን -ሌላ-ይህን

---

[42] *Id.* የ'The Student Fair Access to School Amendment Act of 2018'፣ የ'D.C. Law 22-157'፤ እንደሚተረጉመው ከሆነ የ "ዲሲፕሊን በትምህርት ቤት-ገብቶ አለመማር (disciplinary unenrollment)" እንደ መባረር (expulsion) ወይም ከለፍላጎት ከትምህርት ቤት ተማሪዎ መዛወር፤ አድርጎ ይተረጉመዋል። (D.C. Official Code § 38-236.01(3))

[43] *Id.* የ'The Student Fair Access to School Amendment Act of 2018'፣ የ'D.C. Law 22-157'፤ እንደሚተረጉመው ከሆነ የ "ዲሲፕሊን በትምህርት ቤት-ገብቶ አለመማር (disciplinary unenrollment)" እንደ መባረር (expulsion) ወይም ከለፍላጎት ከትምህርት ቤት ተማሪዎ መዛወር፤ አድርጎ ይተረጉመዋል። (D.C. Official Code § 38-236.01(3))

[44] *Id.* የ'The Student Fair Access to School Amendment Act of 2018'፣ የ'D.C. Law 22-157'፤ እንደሚተረጉመው ከሆነ የ "ዲሲፕሊን በትምህርት ቤት-ገብቶ አለመማር (disciplinary unenrollment)" እንደ መባረር (expulsion) ወይም ከለፍላጎት ከትምህርት ቤት ተማሪዎ መዛወር፤ አድርጎ ይተረጉመዋል። (D.C. Official Code § 38-236.01(3))

[45] *See* D.C. Official Code § 38-236.04(c).

ሁኔታ ሊያስቀር የሚችል ነገር እስካልተወሰደ-ድረስ፤ ከሰላሣ (30) ፈቃድ ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences) በላይ - ከተጠራቀመ፤ በዚያ የትምህርት ዓይነት - የውጤት ደረጃ ለማግኘት በአስጊ-ሁኔታ ላይ መገኘታቸውን የሚገልጽ-የመጀመሪያ የጽሁፍ ማስታወቂያን ያገኛሉ።[46]

- በማንኛውም-ክፍል ውስጥ የሚገኙ ከአስር-አምስት (15) ፈቃድ ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences) ያላቸው የሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎች፤ የ"FA" (በመቅረት ምክንያት የወደቀ/failure due to absences) የሚለውን፤ ከሰላሣ (30) ፈቃድ ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences) በላይ - ከተጠራቀመ፤ በዚያ የትምህርት ዓይነት - የውጤት ደረጃ ለማግኘት በአስጊ-ሁኔታ ላይ መገኘታቸውን የሚገልጽ-ተጨማሪ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያን ያገኛሉ።[47]
- በአንድ ሙሉ የትምህርት ዓመት ውስጥ - በኮርሱ፣ ከሰላሣ (30) ፈቃድ ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences) በላይ - ያጠራቀሙ የሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎች፤ በኮርሱ ክሬዲት የማጣት (loss of course credit) ሁኔታን ከሚያስከተልው ጋር፤ በዚያ ኮርስ የመውደቅ-የመጨረሻ የደረጃ ውጤትን ያገኛሉ።[48]
- በትምህርት ዓመቱ ውስጥ - ከሰላሣ (30) ፈቃድ ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences) በላይ - ያጠራቀሙ የሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎች - ወደሚቀጥለው ክፍል ሊዘዋወሩና ሊያልፉ የሚችሉት፤ በርዕሰ መምህሩ ለቻንስለሩ - ምክንያቱ-ምን እንደሆነ የሚያረጋግጥ ጽሁፍን ማስገባት ከቻሉ፣[49] ወይም ተማሪው በበጋ (summer) ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ መማር ከቻለ እና እንደገና ለማለፍ-ዳግም ግምገማ ከተደረገለት ብቻ-ነው።[50]

### I. ለሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎች፤ አርፍዶ መድረስ (Late Arrival)

ተማሪዎች እንደ አርፋጅ (tardy) ሆነው-የሚመዘገቡት - ይፋ-ሆኖ ክፍለ-ጊዜን ከመጀመሪያ ጊዜ በኋላ - ወደ መማሪያ-ክፍላቸው አምስት (5) ደቂቃዎችን ወይም ከዚያ በላይ አርፍደው-ከደረሱ ነው።

- በአካል-ተገኝቶ (in-person) የትምህርት-አሰጣጥ በሚከናወንባቸው ቀናቶች ላይ፤ አስተማሪዎች - በእያንዳንዱ የክፍል ማለቂያ-ላይ ተማሪዎች መኖራቸውን ምልከታ ማድረግ-አለባቸው፤ ይህ የሚሆነው አርፍደው-የመጡ ተማሪዎች እንደ-አርፋጅ እንጂ እንደቀሩ-ተደርጎ እንዳይመዘገብ ነው።
- አርፍደው-ወደ ክፍል የገቡ ተማሪዎች፤ ከቀሪው-ክፍል ጋር የሚሰሩትን ትምህርት ላይ ተከታትለው ከሌሎቹ እኩል-ሆነው እንዲሰሩ ግልጽ-የሆነ መመሪያ ሊሰጣቸው ይገባል።
- በምንም-ጊዜ ቢሆን ተማሪዎች ከኮርሱ የጊዜ-ሰሌዳ በኋላ ቢደርሱም፤ ወደክፍላቸው ገብተው እንዲማሩ መፈቀድ-አለበት።
- በክፍል-ውስጥ ያለ-ማንኛውም አርፋጅነት (tardy) - ወደ መቅረት (absence) ሊቀየር-የሚችልበት ምንም-አይነት ደረጃ-አይኖረውም። ተማሪው የክፍሉን ከፊል-ብቻ ከተካፈለ፤ እርሱ ወይም እርሷ - የተገኘ/ች (present) እና አርፋጅ (tardy) ሆኖ/ና ከግምት-ውስጥ ይገባል/ትገባለች።
- ተማሪዎች፤ ሁልጊዜ ስራቸውን የማካካሻ (make-up ማድረግ) የሚችሉ-ይሆናል።
- በርካታ-ተማሪው እንዲያረፍድ ያደረጉት ሁኔታዎች፤ እንደ መቅረት (absence) በአንድ-ላይ ተዳምረው አይቆጠሩም።
- ለተማሪው አርፋጅነት የሚሰጡ ምላሾች፤ ተገቢ እና ጥሩ-ምክንያት ያላቸው መሆን አለባቸው። ተማሪው፤ በአርፋጅነቱ - ከትምህርት ቤት ሊታገድ (suspend ሊደረግ) አይችሉም።

### J. ለሁሉም-ተማሪዎች፤ ቀደም-ብሎ መለቀቅ (Early Dismissal)

DCPS፤ ይህ መለቀቅ (dismissal) - ከፈቃድ-ያገኘ መቅረት (excused absence) ጋር ግንኙነት ከሌለው-በስተቀረ፤ የተማሪዎችን ቀደም-ብሎ መለቀቅ (early dismissal)ን፣ እውቅና-አይሰጥም። ቀደም-ብሎ መለቀቅ (early dismissal) በሚያስፈልግ-ጊዜ፤ ወላጆች - ትምህርት ቤቱን ማሳወቅ አለባቸው።

---

[46] 5-B DCMR § 2103.4.
[47] 5-B DCMR § 2103.5.
[48] 5-B DCMR § 2103.6.
[49] D.C. Official Code § 38-781.02(c)(2).
[50] D.C. Official Code § 38-781.05.

## V. ፖሊሲውን ለማስፈጸም የሚፈለጉ መስፈርቶች

ሁሉም የDCPS ተቀጣሪ-ሠራተኞች፤ በዚህ በተቀረጸው ፖሊሲ መስፈርቶች መገዛት ያስፈልጋቸዋል። አፈፃጸሙን ለመደገፍ፣ የሚፈለጉትን እንቅስቃሴዎች እና የጊዜ-አቀማመጥን በዓመታዊ አሰራሩ መሠረት፤ ሁሉም ሠራተኞች እንዲያውቁት ማድረግ፣ ከርዕሰ መምህራኖች ይጠበቅባቸዋል። የዚህ ፖሊሲ አፈፃፀም፤ በመደበኛ የመረጃ ስብስብ (data) ምልከታዎች፣ የመዝገብ ናሙናዎች፣ ከስር ያሉ ሰነዶች ላይ ምልከታ በማድረግ፣ እና በታዎችን መጎብኘት -እንደ አስፈላጊነቱ-፤ እነዚህን ሁሉ ያካተተውን፣ በማዕከላዊ የበላይ ክትትል ሂደት አማካኝነት ተጠናክሮ ይካሄዳል። ይህ ማዕቀፍ (framework)፣ ሁላችንም በአንድነት ቀጣይነት ያለው ማሻሻያዎችን እና አለመገዛትን-የሚከላከል ዘዴን እንድንገነባ ያረጋግጥልናል። ቁልፍ ለሆነ መመሪያ እና እርዳታን-ከጥያቄዎች፣ ከስልጠና ወይም ከማስፈጸም ጋር ለማግኘት-ከፈለጉ፣ እባክዎን dcps.dc.gov ጎብኙ።

DCPS፤ እያንዳንዱን ተማሪ፤ በፍሀታዊነት፣ የላቀ-በላጭነት ባለው አሰራር፣ በግልጽነት፣ እና ተጠያቂነት ባለው-ሁኔታ ለማገልገል -ቁርጠኝነቱን ያሳያል። ማንኛውም ስጋቶች ወይም ስለዚህ ትዕዛዝ መስጫ ላይ ስለሚገኙት ጥሰቶች የበለጠ-ለማሳወቅ፤ የሃቀኝነት ሹሙ ዋና የሆነው (Chief Integrity Officer)ን ለማነጋገር፤ የኦንላይን-መምሪያ (Online Referral) ቅጽን፣ በhttps://dcps.dc.gov/page/office-integrity በመሙላት ወይም ወደ dcps.cio@dc.gov ኢሜል መላክ-ትችላላችሁ።

## VI. የማዕከላዊ አገልግሎቶች የመረጃ-ምንጮች፤ ለትምህርት ቤት አመራሮች

### A. በትምህርት-ገበታ መገኘትና አለመገኘት (Attendance) እና የመቅረት (Truancy)፤ ጥያቄዎች

ቁልፍ-ለሆነ መመሪያ እና እርዳታ - ከጥያቄዎች፣ ስልጠና፣ ወይም አፈፃፀም ጋር ለማግኘት፤ የማዕከላዊ አገልግሎቶች - በእናንተ ክለስተር (cluster) የተመደበውን - በትምህርት-ገበታ የመገኘት የመገናኛ-ክፍል ሠራተኛ (Central Services attendance point of contact)ን፣ እባካችሁ አነጋግሩ። ተጨማሪ እገዛን ለማግኘት ወይም የእናንተን ክለስተር (cluster) የግንኙነት-ክፍል ሠራተኛ ማወቅ ከፈለጋችሁ፤ እባካችሁ - በትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘት (Attendance) እና የእርዳታ አገልግሎቶች ዳይሬክተር - የሆኑትን፣ አንድሪአ  አለን (Andrea Allen)ን በAndrea.Allen@k12.dc.gov እባካችሁ አነጋግሩ።

### B. በትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘት የመረጃ-ስብስብ ማስገቢያ (Attendance Data Entry

በትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘት የግንኙነት-ሠራተኛው (Attendance POC)፤ የትምህርት ቤት-ደረጃን የጠበቀ በትምህርት-ገበታ መገኘት መረጃን በአስፐን (Aspen) ላይ ትክክለኛነቱ መጠበቁን - የማረጋገጥ ኃላፊነት-አለባቸው። የትምህርት ቤት ርዕሰ-መምህራኖች፤ የትምህርት ቤት ደረጃን የጠበቀ በትምህት-ገበታ መገኘት ትክክለኛነቱን - የመጨረሻ-ማረጋገጫ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው። የተማሪ በትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘት የመረጃ-ስብስብ (data)ን በማስገባት (entry) እና በመጠብቅ ላይ፤ እርዳታን-ለማግኘት፤ በትምህርት ቤት የተመደበውን በትምህርት-ገበታ መገኘት ባለሞያተኛውን - እባካችሁ አነጋግሩ። ከአስፐን (Aspen) ጋር ቁልፍ-የሆኑ መመሪያ እና እርዳታዎችን ለማግኘት፣ እባካችሁ - የእርዳታ-ጠረጴዛ (Helpdesk)ን በ202-442-5717 አነጋግሩ።

## አባሪ (Appendix) A: ለሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎች፣ የርቀት (Virtual) የትምህርት አሰጣጥ

ለትምህርት ዓመት 2022-23፤ DCPS - የርቀት (virtual) የትምህርት አሰጣጥን፣ ለተወሰኑ ቁጥር-ላላቸው የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፤ ይሰጣል። የርቀት (virtual) መማር ፕሮግራሙ፤ በDCPS - የኦፖርቹኒቲ አካዳሚስ/Opportunity Academies በሆኑት ብቻ (Luke C. Moore, Ballou STAY, and Roosevelt STAY) የሚሰጥ፣ እና ከ9-12 ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ ማንኛውም ፍላጎት ያለው ተማሪ - መጀመሪያ-ቀድሞ ለመጣ መጀመሪያ አገልግሎት በመስጠት-አሰራር መሠረት (እስከ 200 ለሚደርሱ ተማሪዎች) የሚገኝ-ይሆናል። በፕሮግራሙ ውስጥ ያሉት የርቀት (Virtual) ተማሪዎች፤ ከሦስቱ በአንዱ የ'OA' ፕሮግራሞች በሆኑት ውስጥ (ይህን የትምህርት ቤት መዝገባቸው በሚሆነው-ውስጥ) ተመዝግበው-የሚማሩ ይሆናል። በተጨማሪም፤ በርቀት (virtual) ፕሮግራም[51] ውስጥ በጣምራ-ምዝገባ የሚመዘገቡም-ይሆናል። በዚህ ለተወሰነ-ጊዜ የርቀት (virtual) አማራጭ ስለሆነው-የብቁነት መስፈርቶችን ጨምሮ፣ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፤ በhttps://dcps.dc.gov/page/opportunityacademy ላይ መገኘት-ይችላል።

የርቀት የትምህርት-አሰጣጥ (virtual instruction)ን የሚያገኙት - የርቀት (Virtual) ተማሪዎች፤ በየቀኑ-በትምህርት ገበታ ተገኝተው መማር (በመደበኛ ወይም መደበኛ-ባልሆነ የትምህርት አሰጣጥ/synchronous or asynchronous) ከተመደበላቸው-አስተማሪዎች ጋር በመሆን በተመደበው የኮርስ የጊዜ-ሰሌዳዎች መሠረት መማር-ያስፈልጋቸዋል።

### A. የተማሪን በትምህርት-ገበታ መገኘትና አለመገኘት (Attendance)ን መመዝገብ

በOSSE 5-A DCMR § 2101.12 - የአስቸኳይ-ጊዜ እና ሃሳብ-የቀረበበት የደንብ-አወጣጥ ላይ መሠረት-በደረገ፣ እና በመጨረሻ የደንብ-አፈጻጸምን በመጠባበቅ-ላይ፤ ተማሪዎች "መገኘታቸውን/presence" ለማረጋገጥ፤ በ'roll call' ወቅት - ካሜራዎቻቸውን እንዲያበሩ-ይጠየቃሉ።[52]

ተማሪው - መደበኛ ባልሆነ-መንገድ የሚሰጠውን የትምህርት አሰጣጥ (synchronous instruction)ን ሙሉ-ለሙሉ ወይም በከፊል የሆነው የትምህርት-ቀን ውስጥ እንዳይካፈል የሚከለክለው - የቴክኖሎጂ ወይም የኢንተርኔት ማገናኛ ችግሮች ካሉት፤ ተማሪው ወይም ወላጆቹ ወይም አሳዳጊውወዲያውኑ ወደ ትምህርት ቤታቸው መደወልእና ችግሩን ሪፖርት ማድረግ እና ተማሪው በምን ላይ በዚያ ዕለት ላይ እየሰራ-እንደሆነ ለማሳወቅ ማነጋገር አለባቸው። የ 'AC/AD'ው፣ "የአስቸኳይ-ጊዜ (Emergency/ሌላ ፈቃድ-ያገኘ (Other Approved)" ኮድ (code)ን ለማንኛውም በዚህ ምክንያት የተማሪው የሚያመልጠውን ክፍሎች፤ የሚያስገባ-ይሆናል። ተማሪዎች የርቀት (virtual) የትምህርት-አሰጣጡን ከማግኘት የሚከለክሏቸውን ማንኛውንም የቴክኖሎጂ ችግሮች ለመፍታት-ትምህርት ቤቱ ወዲያውኑ ከቤተሰቦች ጋር መስራት አለበት።

### B. ከትምህርት ቤት አለመገኘት (Absences)

ለርቀት (virtual) ተማሪዎች፤ የመቅረት-ሁኔታዎች (Absences) - በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት የግንኙነት-ክፍል ሠራተኛው (attendance POC) አማካኝነት ምልከታ-የሚደረግለት እና፣ እንደ "excused" ወይም "unexcused" በሚል-በዚህ ፖሊሲ ላይ ባለው 'section C.2' መሠረት ኮድ (code) የሚሰጡት-ይሆናል። ሆኖም-ግን፤ ቤተሰቡ - በቴክኖሎጂ በሚያጋጥሙት አስቸጋሪ-ሁኔታዎች፣ በኤሌክትሮኒክ-ሰነዶችን ማስገባት ካልቻለ፤ የትምህርት ቤት በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት የግንኙነት-ክፍል ሠራተኛ (attendance POC)ን በማነጋገር፣ የሰነዶቹን ሁኔታ ለመግለጽ እና ወደ ትምህርት ቤቱ የሚገቡትን ሰነዶች ቅጂ - የጤና ሁኔታዎች በሚፈቅድ-ጊዜ፣ ታትሞ (hard copy) ከተጠየቀ-እንዲያቀርቡ ማነጋገር አለባቸው።

---

[51] የDCPS የኦፖርቹኒቲ አካዳሚስ (opportunity academies)፤ (ለምሳሌ፤ Roosevelt STAY, Luke C. Moore) በአካል-ተገኝቶ (in-person) እንቅስቃሴዎችን - እንዲሰጣቸው ለጠየቁ-ተማሪዎች መስጠት አለበት፤ ነገር-ግን ተማሪዎች የርቀርት (virtual) መማርን ሊመርጡ-የሚችሉ እና ይህን ለማድረግ የህክምና ሰርቲፊኬት ሂደት መስፈርትን-ማሟላት አያስፈልጋቸውም።

[52] ፍትሃዊ-እኩልነት (equity) እና የግላዊ (privacy) ሁኔታዎን ለመደገፍ፤ ከኋላ-የሚታየውን (background) እንዴት ማደብዘዝ እንደሚችሉ፣ ወይም ሌላ አማራጭ ከኋላ የሚታይ-ምስል (background) መጠቀም እንደሚችሉ - ግልጽ-የሆነ የመመሪያ ትዕዛዞች ሊሰጣቸው ይገባል።

### C. በትምህርት-ገበታ ላይ ያለመገኘት (Attendance) - ጣልቃ-ገብነቶች/Interventions

በ'Section F' ከላይ በተገለጸው የትምህርት ገበታ ላይ ያለመገኘት ጣልቃ-ገብነቶች (attendance interventions) - መደበኛ-አሰራር በተጨማሪ፣ የAC/AD በተጨማሪ - የደህናማ-መሆን ምልከታ-ማድረጊያ የስል ጥሪ (phone call)ን - ተማሪው ወደ ሦስት (3) ፈቃድ ያላገኘ በትምህርት ገበታ ላይ አለመገኘት (unexcused absences) ላይ ሲደርስ፤ ማንኛውም ቴኪኒካል እንቅፋቶች መኖራቸውን ለመለየት ወይም ሌላ አስቸጋሪ የሆኑ ነገሮች ገጥመው ከሆነ የሚከታተል እና የስልክ ጥሪው (phone call)ን ውጤት በአስፐን የግንኙነት ጆርናል (Aspen communication journal) ላይ በመዝገብነት-ያስቀምጣል።

## አባሪ (Appendix) B: ተገልሎ-መቆየት (Quarantine) እና ራስን-መለየት (Isolation)

የጤና መመሪያ ባለበት እና ተለዋዋጭ የሆኑ የጤና ሁኔታዎች በሚፈጠሩበት ጊዜ፤ ተማሪዎች ተገልለው-የሚቆዩበት (quarantine) ወይም መለየት (isolate) ማድረግ የሚያስፈልጋቸው ጊዜያቶች ሊኖሩ ይችላሉ።

አሁን-ባለው የጤና መመሪያ መሠረት - ተማሪዎች እራሳቸውን-አግልለው (quarantine) ወይም ተለይተው (isolate) አድርገው መቆየት በሚያስፈልጋቸው ጊዜ፤ ወላጆች ፈቃድ-የማግኛ ማስታወሻን - በዚህ ፖሊሲ Section C.1 ላይ በተዘረዘረው መስፈርቶች አማካኝነት - ማስገባት አለባቸው። ሕጋዊ-የሆነ ፈቃድ-የማግኛ ማስታወሻ ያላቸው፣ ሁሉም - ተገልሎ-መቆየት (quarantine ) እና የመለየት (isolation) መቅረቶች፤ እንደ ሕመም-ተብሎ **'ፈቃድ-/excused'** ያገኛሉ።

ከዚህ በታች ያለው ዘንጠረዥ የሚያሳየው፤ ተማሪዎች ተገልለው (quarantine) ወይም ተለይተው (isolate) መቆየት ሲያስፈልጋቸው፤ በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘቱ (attendance) እንዴት ኮድ (code) እንደሚሰጠው ያሳያል።

| ተማሪ-የሚከተለው ከሆነ: | ወዲያውኑ የሚከተለው መደረግ-አለበት: | በ5ኛው ቀን ወይም ከዚያ በኋላ ባለው-ጊዜ፤ የሚከተለው መደረግ-አለበት: |
|---|---|---|
| ለCOVID-19 ምርመራ-አድርጎ - ቫይረሱ እንዳለ (positive የሆነ) እና አነስተኛ-የሆነ/mild ወይም ምንም-ምልክቶች የሌለው። | ቢያንስ ለ5 ቀናቶች ተለይቶ-መቆየትን የጀመረ። | ተማሪዎች፤ ለ24 ሰዓታት - ማንኛውን የመከላከያ መድሃኒትን ሳይወስዱ እና ምልክቶች እየተሻሻሉ መጥተው - ከትኩሳት ነፃ ሆነው የቆዩ-ከሆነ፤ ከ6ተኛው ቀን ጀምሮ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ ይችላሉ።<br><br>ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በሚሆኑ-ጊዜ፣ የምርመራ-ውጤቱ ቫይረሱ እንዳለ (positive) የሆነ፣ ወይም ምልክቶች-ማሳየት ሲጀምሩ - የትኛውም-ቢሆን ቀድሞ-የመጣው፤ እስከ 10 ቀን ድረስ የፊት-መሸፈኛ ማስክ (mask) ማድረግ አለባቸው። |
| ለCOVID-19 ቫይረሱ-እንዳለ (positive) የምርመራ-ውጤትን ያለው፣ እና ከሁለቱ-አንዱ፤ (1) ጠንካራ-የሆነ ወይም አደገኛ-የሆኑ ምልክቶች ወይም (2) በሽታን-የመቋቋም አቅም-የሌለው መሆኑ የታወቀ (immunocompromised የሆነ)። | ቢያንስ ለ10 ቀናቶች ተለይቶ-መቆየትን መጀመር። | ተማሪዎች፤ ለ24 ሰዓታት - ማንኛውን የመከላከያ መድሃኒትን ሳይወስዱ እና ምልክቶች እየተሻሻሉ መጥተው - ከትኩሳት ነፃ ሆነው የቆዩ-ከሆነ፤ ከ10ኛው ቀንበኋላ ወደ ትምህርት ቤት ሊመለሱ-ይችላሉ።<br><br>ተማሪው፣ ከአስር ቀናቶች በላይ ከትምህርት ቤት ውጪ የሚሆን ከሆነ፤ ቤተሰቦች - የሐኪም ማስታወሻ ወረቀንት ለትምህርት ቤታቸው - ለመቅረቱ-ፈቃድ እንዲያገኝ ማቅረብ ያስፈልጋቸዋል። |
| ለCOVID-19 ቫይረሱ እንዳለው (positive ከሆነ) ግለሰብ ጋር  የቅርብ-ንክኪ ያለው፤ ሆኖ ተልይቶ ነበር። | ተገልሎ-መቆየት (quarantine ማድረግ) አያስፈልግም። | ከተጋለጡበት ቀን ጀምሮ፤ ተማሪዎች ለ10 ቀን በትምህርት ቤት ውስጥ የፊት-መሸፈኛ ማስክ (mask) እንዲያደርጉ-ይበረታታሉ። ተገልሎ-መቆየት (quarantine ማድረግ) አያስፈልግም። |